ከገዳሙ ድረስ እመጣለሁ ሲል አዘዘኝ:: መጣሁ:: የሰኔ ማርያም ደግሞ መርሻ ይመጣል:: ፈጣሪዬ ከረዳኝ እጄ ወደ ነበረበት ጤንነት ይመለስ ይሆናል ሲል ተስፋ ሰነቀ:: እኔም ችግሩን ሲነግረኝ እያዘንሁ ቆብና ቀሚሱን ሰፍቼ አለበስሁት:: ምናኔው ከወዲሁ ሠመረለት:: የምናኔ አጀማመሩ ሰወግ አይመችም ነበር:: ፍጹም ትሑት መናኒ ሆነ:: እየቆየ አንድ ነገር ቅር አለኝ:: ሰውዬው ሰኔ ማርያም ከመርሻ ጋር የነበረው ቀጠሮ አሳሰበኝ:: በሰኔ የሚመጣው መርሻ ወይስ መልአከ ሞት? እያልሁ ውስጤን ስጠይቅ በጋው አለፈ:: ፀደይ ገባ:: የጸደይ ነፋስ እንዳልተስማማው ግልጽ ነበር:: ገና በመጋቢት እኩሌታ የጸደይ ኮከብ ሲወለድ ጀምሮ ጤናው ይበልጥ እየተቃወሰ ሄደ:: በሰኔ ማርያም ግን የፈራሁት ነገር ደረሰ:: ከመርሻ ቀድሞ መልአከ ሞት መጣ:: ሰውየው የሰኔ ማርያም ዕለት አረፈ:: ከዚች ቀን ጀምሮ የመርሻ መንፈስ ምን መንፈስ እንደሆነ ሳስብ እኖር ነበር:: በኋላ የረር ተራራ ላይ ተገናኘን:: አመጣጡ ይህን የሕዝብ እሳቤ ተሸክመው እንደኔው ቴዎድሮስን መፈለግ ነበር::" ብለው ከተረኩ በኋላ ከዶቅማው ሥር ተነሥተው ወደ ወይራው ቀጠሉ::

ከርታታው ታሪኩ ወጉ ውስጡን እንደጨበጠው ይታወቃል:: ከንፈሩ በብርድ ቢዝልም አእምሮው እንደተሳለ ነው:: በደንብ ይሰማል:: አልፎ አልፎ ደግሞ ይመዘግባል:: በስዋሬ ካሉ





ጠቢባን ጋር የመኖር ፍላጎቱም ሰማይ ደርሷል:: በዚህ ስፍራ ውስጥ ተዋነይ መልአከ ሞትን የገዘተበትን ምሥጢር ለማወቅ ያለው ጉጉት ውጣ ውረዱን አቅልሎታል:: የሞት መግቻውን መና እስኪቋደስ ዓመት ሁኖበታል::

"የረር ስደርስ ቀድሞ የገባው መርሻ ነበር:: በእንግዳ ልማድ ተኮፍሶ አገኘሁት:: እሱ መሆኑን ስሰማ ቀረብሁት:: አንድ ሌሊት አፍ ላፍ ገጥመን ስንጫራት አደርን::" ብለው ወደ ቴዎድሮስ ታሪክ ሲያልፉ ሲንደረደሩ

"ገዳም ጠብቀኝ ተብሎ መርሻን ሲጠብቅ ስለነበረው ሰው ታሪክ አንሥተው ጠየቁ?" አለ ገሞራው::

"ምኑ ይጠየቃል! ሰውዬው አንድ ጊዜ የገዳም አፈር ቀምሷል:: ያን ታሪክ ለመርሻ ማንሣት አስፈላጊ አልነበረም:: አልጠየቅሁም::" አሉ::

"ምን አልባት የሰውን እድል ፈንታ የሚያውቁበት ነገር ካላቸው ብዬ ነው::" አለ ገሞራው::

"እሱማ አለው:: መንፈሱ የምን መንፈስ እንደሆነ ግን ግልጽ አይደለም:: ርኩስ መንፈስ ይሁን ቅዱስ መንፈስ ራሱ መርሻም የሚያውቀው አይመስለኝም::" አሉ ዐራት ዐይናው::

"እንዲህ ዐይነቱን መንፈስ መርምሮ ከፉውን ከደጉ መለየት መልካም ይመስለኛል:: ጠይቀዋቸው ቢሆን አሁን ተረጋግተው ይመራመሩበት ነበር::" ሲል ታሪኩም ጥያቄውን ደገመው:: "ወቅቱ ይህንን ለመጠየቅ አመቺ ወቅት አልነበረም:: በየረር እልፍ ጆሮ ጠቢዎች ነበሩ::

እኔ እየተሰወርሁ ዘወር ዘወር ስል መርሻ እንደኔው ባይሰወርም ከአጠገቡ ያሉ ጆሮ ጠቢዎችን የሚለይበት ነገር ግን ነበረው::" አሉ ዐራት ዐይናው::

"እረ በማርያም!" አለ ገሞራው እንደመባነን ብሎ::

"እውነቱን ነው:: በዚያች አጭር ቀን ያንን ሲያደርግ አይቸዋለሁ:: ምን መሰላችሁ? ሰላዮች ከሴትም ከወንድም ወገን ነበሩ:: በሴቶች በዓት ሴት ጆሮ ጠቢዎች፣ በአባቶች በዓት ደግሞ ወንዶች መናንያን መስለው የረርን ወረውታል:: እኔና መርሻ ጨዋታ ስንጀምር አንዲት ሴት መሰስ ብላ መጥታ ይፍቱኝ ይባርኩኝ አበስኩ ገበርኩ ብላ ከእኔ ሥር ወደቀች:: ከመካከላችን ጆሮ ጠቢ መሣሪያ በድብቅ ታስቀምጥና ኋላ ታነሣዋለች አሉ:: እኔ ይህንን አላውቅም ነበር:: መሣሪያው ዘመኑ ያመጣው ጆሮ ጠቢ መሣሪያ ነው ሲሉ ሰምቼ አዝኛለሁ:: ሴቷ አበስኩ ገበርኩ ይፍቱኝ ስትልማ መርሻ ሆዬ "በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ





ወዲያ ሂጅ ይቺ ሰላቢ! ጆሮ ጠቢ አንቺ ሰላቢ! ሂደሽ ከተማውን ስለቢ "ይቺ ሰላቢ! ሰላቢ! ሰላቢ! ጆሮ ጠቢ! ሰላቢ ጆሮ ጠቢ!" ሲላት ከዚያው የተሰበሰበው ሕዝብ መርሻን ተከትሎ

"ሰላቢ! ጆሮ ጠቢ!

ሰላቢ ጆሮ ጠቢ! ሰላቢ! ጆሮ ጠቢ!" እያለ ጨፈጨፋት:: ጨፈረባት:: ይቺ ሴት ገዳም ለገዳም እየዞረች አበው እንዲደበደቡ አድርጋ ኑሯል መሰል ያን ቀን ፈጣሪ አጋለጣት:: መርሻን ጣለባት:: እሷም መሰስ ብላ ሄደች:: ጥቂት ቆይቶ አንዲት አውሮፕላን ድምፅ ሳታሰማ መጥታ ዱቅ አለች:: ከዚያ የተሰበሰበው ሕዝብ በቁሙ ሞተ:: ከንዱ የፈረጠመ ወታደር ያንን ሁሉ ሕዝብ በዱላ እየወቃ መኪና መጥቶ እስኪወስደው ድረስ የኋሊት ከነቸረው:: አፍታ ሳይቆዩ ሦስት ጥቁር ጥቁር መኪናዎች ተወንጭፈው ገዳሙ ድረስ ብቅ አሉ:: መርሻ ተንከባሎ ጉድጓድ ገባ:: ወታደሮች አጥብቀው እየፈለጉት ነበር:: መገኘቱን ላረጋግጥ አልቻልሁም::" ብለው ዝም ሲሉ

"እርስዎስ ከወዴት ተጠጉ?" አለ ገሞራው::

"እኔማ የተዋነይን ሥራ ሠራሁ፡፡ ተሰወርሁ፡፡ እኔ ስሰወር ሴቷ ዋናው አማቂ ገና አልተያዘም፡፡ ፈልጉት፡፡ እሱ ከእጃችን ካልገባ ከዚች ንቅንቅ ማለት የለም እያለች ጥብቅ መመሪያ ስትሰጥ ከሩቅ ቁጭ ብዬ እያዳመጥሁ ነበር፡፡ እኔን ፍለጋ ያልተመነቀረ ዋሻ አልነበረም፡፡ መንቅረው መንቅረው ሲያጡኝ አባቶችን ዐሥረው እየደበደቡ ወደአዲሳባ ከተማ ሄዱ፡፡ በነጋታው ከስዋሬ ወጣ ብዬ ዘወር ዘወር ስል አንድ ወታደር ከድንጋዩ ጋር ድንጋይ መስሎ ያደፍጣል፡፡ ከአጠገቡ ደርሼ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ እኔ እንጅ እሱ አላየኝም፡፡ ኮቴዬን ሰምቶ ቀና ሲል እኔ የለሁም፡፡ ወደ ስዋሬዬ ተመለስሁ፡፡ ሂደ በጊዜው ለነበረው መሪ ቴዎድሮስን አይቸው ነበር፡፡ እርምጃ ልወስድበት ስል ተሰወረ፡፡ ይህንን በተደጋጋሚ አረጋግጫለሁ ብሎ ተናገረ፡፡ ከዚያ ወዲያ የረር ተራራ የወታደሮች ምሽግ መሆን ጀመረች፡፡ አሁን ድረስ ሰው ቴዎድሮስ በየረር ዋሻ ተሰውሮ ይኖራል የሚለው እኔን ነው፡፡ መንግሥት የረርን በጥርጣሬ ዐይን የሚመለከትበት ታሪክ ይህንን ይመስላል፡፡" ካሉ በኋላ ፈገግ ብለው

"በዚህ ዘመን ያለው ትውልድ ተሰወረ፡፡ ተገለጠ፡፡ ቴዎድሮስ የረር ውስጥ ይወጣል የሚለው ይህንን የእኔን ቁንጽል ስዋሬ ይዞ ነው፡፡ በየረር ስገለጥ ስሰወር የነበርሁት እኔ ራሴ ነኝ፡፡ እኔ ግን ቴዎድሮስ አይደለሁም፡፡ ልሆንም አልችልም፡፡





ወደፊት የሚመጣውን ግን አላውቅም፡፡ አንዱ ሲመጣ ስመ መንግሥቱን ቴዎድሮስ ሊለው ይችላል፡፡ የሆነ ሆኖ አሁን አሁን የሀገሬ ሰዎች ቴዎድሮስ ከየረር ተራራ ይወጣል ሲሉ ያወራሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ በመልክ ሳይቀር አይተነዋል ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ መንግሥትም በዚህ በኩል ብዥታ ተፈጥሮበታል፡፡ ይኸውም ሊታወቅ ተራራውን በታጠቁ ሠራዊት እያስጠበቀው ነው፡፡ ከየረር ታች የተኮለኮሉ ሠራዊቶች ቴዎድሮስ ዘሎ ቤተ መንግሥት እንዳይገባ እየጠበቁ ነበር፡፡ አቤት ፍርሐት! ቂቂቂ በዚች ምድር ሥልጣን እንደያዘ ሰው ፈሪ የለም፡፡ ቂ! ቂ! ቂ!" ብለው "እኔ ግን በወቅቱ ቴዎድሮስ ከየረር እንደሌለ አረጋግጬ ተመለስሁ፡፡" ብለው ሲስቁ ከቆዩ በኋላ

"መቼስ ምኑን ተናግሬ ምኑን እደብቃችኋለሁ፡፡ የረር ውስጥ በስዋሬ ሳለሁ መናው አብሮኝ ነበር፡፡ ለጊዜው ዋሻ ውስጥ ሁኜ ሰዎች ከአዲሳባ እያመጡ በየዋሻው በር የሚያስቀምጡት ጥራጥሬ ነገር አለ፡፡ እሱን እየቆላሁ ተመገብሁ፡፡ እየቆየ ግን ወታደሮች እየበዙ ጥበቃው እየተጠናከረ መጣ፡፡ እኔም ምን አልባት ቴዎድሮስ በስዋሬ ካለ ብዬ ለዓመት መቆየቴ ያኽል አልቀረም፡፡ በዚያ ስቆይ የመናውን ቁራሽ መመገብ ጀምሬ ነበር፡፡ መናው መኻል

ሀገርም ይበላል፡፡ እኔ በራሴ ተመግቤዋለሁ፡፡" ብለው ከወይራው ቤት ሲደርሱ ጥቂት ሲቀራቸው

"ታዲያ ቴዎድሮስ ከዚሁ ደቅ እስጢፋ ይወጣ ይሆን?" አለ ገሞራው

"እንዴት ልትገምት ቻልህ?" አሉ ዐራት ዐይናው፡፡

"አሁን ኢትዮጵያ ፍጅት ላይ ናት፡፡ እኛም አንድ ጓደኛችንን ገብረናል፡፡ ዶክተር ነበር፡፡ ዳንጉር ተራራ ላይ በቀስት ወጉት፡፡ ቀስተኞች ደግሞ ጥቁሮች አይመስሉኝም፡፡ ጭምብል አጥልቀዋል፡፡ ከወዴት እንደመጡ አላወቅንም፡፡ ምን አልባት በዚህ አካባቢ ያለው ጦርነት ከቴዎድሮስ ጋር የተያያዘ ጦርነት እንዳይሆን? ቴዎድሮስ በስዋሬ ይኖራል የሚባለው ወሬ አሁንም በመኻል በሀገር እንደጉድ እየተወራ ነው፡፡ በስዋሬ ያለው አዲሱን ንጉሥ ፍለጋ የሚማስኑ የዋሃንም ቀላል አይደሉም፡፡ ተረት ተረቱ ሀገር እየመራ ነው፡፡ የ ንግርት በትክክል የሚደርስ ከሆነ ቴዎድሮስ መወለድ ያለበት ከጠቢባኑ አብራክ ከሆነ ብዬ ነው?" አለ ገሞራው፡፡

ዐራት ዐይናው ከት ብለው ሳቁ፡፡ ሳቃቸው የሽሙጥ ሳቅ ነበር፡፡ ስቀው እንዳበቁ "ይህ የጠቢባን ዓለም የቅዠት ዓለም አይደለም፡፡ የሕልም ንጉሥ አይነግሥበትም፡፡ የሕልም





እንጀራ አይበላበትም፡፡ ምትሐት የለበትም፡፡ የገነት አምሳል ነው፡፡ ሰይጣን ወደዚህ ገብቶ አያጭበረብርም፡፡ ስዉሩ ዓለም የእውነት ዓለም ነው፡፡ በዚህ ውስጥ መጻኢው ቴድሮዎስ ስሙ አይታወቅም፡፡ ያለፈው ዐጤ ቴዎድሮስ ግን በታሪክ ውስጥ ተካቷል፡፡ የመቅደላው ቴዎድሮስ እንጂ የየረሩ ቴዎድሮስ በጠቢባኑ ዘንድ ቅዠት ነው፡፡" ሲሉ በአጭር ከቋጩት በኋላ ታሪኩ ሲያልቅ ከማረፊያቸው ደረሱ፡፡ ከሴቶች የሞት መግቻውን ለማግኘት ሳምንት ቀርቷቸዋል፡፡ እስከዚያ ግን ከዐራት ዐይናው ጋር ሲሰነብቱ ጉባኤው ወስኗል፡፡ በዚያ ላይ የመናው ምሥጢር ባዕድ ነገር እንዳይመስላቸው በደንብ መጠየቅ አለባቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ ዐራት ዐይናው አሉላቸው፡፡ እንደደቀኛው ሁሉም በጉንጫቸው ነው፡፡ ከመኻል ሀገር እስከ ስዉሩ ዓለም ከገጠር እስከ ደብር ከዓለም እስከ ገዳም የማያውቁት የኢትዮጵያ ምሥጢር የለም፡፡ ስለ ተዋነይ ታሪክ ለማጥናት ሀገር ለአገር ተንከራትተዋል፡፡ በተለይ ውዶ ማርያም ከራርመዋል፡፡ ውዶ ማርያም በወረታ በላይ ያለ ሀገር ሲሆን ድሮ የተዋነይ ስእል በዚሁ ደብር ነበር፡፡ ከስዕሉ ውስጥ ያን ነገር ለማየት ሂደው ነበር፡፡ ሀገሬ ሰላምን ዘወር ዘወር ብለውባታል፡፡ ጎንደርን እንደሳቸው በርብሮ የሚያውቃት የለም፡፡ የሰቋር ኪዳነ ምሕረት የጥበብ መጻሕፍት የተፋቀ ቀን ምርር ብለው አልቅሰዋል፡፡ ተከስተ

የሞተ ዕለት አፈር ለመቅመስ ወደመኻል ሀገር ሲመለሱ በጭንቅ ቀርተዋል:: ወይራው ገልግለው ከሞት አትርፈዋቸዋል::

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan) የቴሌግራም ቻናል





# ሽፎ

መሺ በከንቱ

ከዐራት ዐይናው ቀለሙ ማረፊያ ሲደርሱ ልዩ መዓዛ አወዳቸው:: ትልቁ ዋሻቸው በጉም ተወሯል:: ወስደው እንደመኻል ሀገሩ መስተንግዶ ራት አልጋበዟቸውም:: እንዲያውም የመናውን መግቻ እንዳያዩት ይባስ ለውረውታል:: ከአንድ ግዙፍ ዶቅማ ሥር ካለ ዋሻ ከወሸቋቸው በኋላ የዶቅማና የእሼ ፍሬ አቀረቡላቸው:: ደረቅ ማር መረቋቸው:: ገሞራው ስለዚህ ማር ጥቂት ወሬ ሰምቶ ነበር:: በመጀመሪያ “ለልብ ሕማም ፈውስ” ነው ሲሉ የሰማው ትዝ አለው:: ሁለተኛው ልጅ መውለድ እምቢ ያላቸው ሴቶች ከማሩ ሲቀምሱ ማኅፀናቸው ተፈትቶ የልጅ እናት እንደሚሆኑ የሰማው መጣለት:: ከዚያም “ከጥርስ ቁርጥማት ሕማም ይፈውስ ይሆን?” ሲል በውስጡ ተናገረ:: ከዚያም በጥርሱ ነክሶ ለደቂቃ ያዘው:: ጥርሱ “ተሸሸሸሸሸሸ” ሲል ተሰማው:: በቀላሉ ሲፈወስ በፍሥሐ ፈነጠዘ:: ማሩን እየዋጡ ስለ መናው አነሡ:: ጥያቄውን ያነሣው ገሞራው ነበር::

“የኔታዬ” አለ ገሞራው ማሩን ጨርሶ የዶቅማ ፍሬ በጉንጩ እያልጎመጎመ:: ዐራት ዐይናው ቀና ሲሉ ከግም ፊቱ ጋር



Scanned with CamScanner

የዶቅማ ፍሬ አጎራረሱን አይተው ፈገግ አሉ፡፡ ጥሩ ግመሬ ዝንጀሮ ወጥቶታል፡፡

"ትናንት መናውን ሳይ ጥርጣሬ አደረብኝ፡፡ ቅር ያለኝ ነገርም አለ፡፡ እሱ ደግሞ የስዉሩ ዓለም ኀብስተ-መና ከመኻል ሀገር የሚኖሩ በአስማት በኩል የሚታሙ ሰዎች በነፋስ ከሚያመጡት ቁራሽ ጋር ተመሳስሎብኝ ነው፡፡ ግልጽ ለማድረግ አንዳንድ አስማተኞች አስማት ሲደግሙ መና በነፋስ ያመጣሉ ይባላል፡፡ ይህ ከዚያ በምን ይለያል?" አለ ገሞራው ከሰይጣን የሚገኝ ነገር ይሆን? እያለ ሳምንቱን ሲጠራጠር ሰንብቶ፡፡

"ለጥበብ ወጣኒ እንደመሆናችሁ ይህንን መሰል ጥያቄ በተደጋጋሚ ብታነሡ አይፈረድባችሁም፡፡ እኔም እውነተኛውን መና ማሠሥ ስጀምር በነፋስ የመጣ ትኩስ እንጀራ ተመግቤአለሁ፡፡ እውነት መስሎኝ እኔም መኻል ሀገር ሳለሁ ደክሜበታለሁ፡፡ ነገር ግን በነፋስ ቢመጣም ቅሉ ከወዴት እንደሚመጣ ልደርስበት አልቻለሁም፡፡ ከመኻል ሀገር ሳለሁ ግን አንድ ቀን ተመግቤው ነበር፡፡ ለዚህም ደግሞ ንስሓ ገብቻአለሁ፡፡ በነፋስ የሚመጣው ግን ከስዉሩ ዓለም ካለው መና ጋር በፍጹም ተመሳሳይነት የለውም፡፡ ሁለቱንም ስለማውቃቸው ሐቁን እነግራችኋለሁ፡፡" ብለው





እንቅጩን ተናገሩ፡፡ ዐራት ዐይናው ቀለሙ ጥንትም እውነታውን ይደፍራሉ፡፡

"እረ ባዛኚቷ! የመኻል ሀገሩንም ያውቁታል?" አለ ገሞራው በእሱ ድካም ማለፋቸው ግርም ብሎት፡፡

"እናንተ ቅኔ ቤት ሳላችሁ አልሞከራችሁትም? በእኛ ጊዜኮ የቅኔ ተማሪ ኩሸት የሚጀምረው ከዚህ ነበር፡፡" ዐራት ዐይናው ወደ ጥንቱ ተመልሰው አስታወሱ፡፡ የቅኔ ቤቱ ኩሸት ትዝ አላቸው፡፡ መና በነፋስ እናመጣለን እያሉ ሕዝብ ሲያታልሉ የነበሩ ሐሰተኞችን በውስጣቸው ነቀፉ፡፡

"እረ የለም! የለም! በእርግጥ ለእኔ አንድ ሰው ላቅምስህ ብሎኝ ነበር፡፡ ከርኩስ መንፈስ ይሁን ከቅዱስ መንፈስ እንደሚመጣ ሳላውቅ በአፌ አላደርገውም ብዬ እምቢ አልሁኝ፡፡" አለ ገሞራው

"እንዲያ ነው ልጄ! እንኳንም ቀረብህ! እኔም ቀምሸው የጠቀመኝ ነገር የለም፡፡" ብለው ቀጠሉ፡፡

"እኔና መሼ በከንቱ ሞክረነው ነበር፡፡ እኔ ግን እስከ መጨረሻው አልዘለቅሁበትም፡፡ ጀምሬ ተውሁት፡፡" አሉ ዐራት ዐይናው፡፡



Scanned with CamScanner

“ለምን? ምን እንቅፋት ገጠመዎት?” ገሞራው ዐይኖቹን እያስለመለመ ጠየቃቸው፡፡

“ያ ከንቱ ነገር ሲቀር ቀርቷል፡፡ ጥበቡም አስማታዊ ጥበብ ይመስለኛል፡፡ ነው ለማለት ግን አልደፍርም፡፡ የእኔና የመሼ በከንቱ ሙከራ ሲቀር ቀርቷል፡፡ ያን ማንሣት መሸልቸት ነው፡፡ በነገሩ ስለማላምንበት መልሼ መተረክ አልፈልግም፡፡” አሉ ዐራት ዐይናው፡፡

“እረ በማርያም ይንገሩን፡፡ ክፉን ከደጉ፣ የስዉሩ ዓለም መና ከአስማተኞች መና ለይቶ ለማወቅ ያግዘናል፡፡ ክፉ ነገርም ቢሆን ክፋቱን አውቀን እንገድፈዋለን፡፡ ጀምረው አይተውት፡፡ ጥበቡን ያስተምሩን አንልም፡፡ ታሪኩን ግን ይንገሩን፡፡ ባይጠቅመንም አይጎዳንም፡፡” አለ ታሪኩ የኩራት በሚመስል መልካም ድምፅ፡፡

“ከተረሣ ነገር ላይ ጊዜ ማጥፋት መልካም አይደለም፡፡ ያ ሲቀር ቀርቷል፡፡ የስዉሩን ዓለም መና ግን ተፈጥሮአዊ እንደሆነ እመኑ፡፡” አሉ ዐራት ዐይናው፡፡

“ምን አዲስ ምሥጢር ቀረብን እያልን ልባችን ከሚጠራጠር በጥቂቱም ቢሆን ይንገሩና ልባችን ይሻር?” አለ ገሞራው፡፡





ዐራት ዐይናው አጥብቀው እንደያዟቸው ሲረዱ ከሥር ጎለጎሉት፡፡

“ስዉሩን ዓለም ከመቀላቀሌ በፊት ጥበብ አለው የሚባለውን ተራ ሰው ሁሉ መከተል አበዛ ነበር፡፡ ሞጣ ቅኔ ሳለሁ ነው፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን የቀለምና የጥበብ አባቴ ወደደጋው ለልቅሶ ይዘውኝ ወጡ፡፡ ከዋሸራ ራስጌ ልቅሶ ሄድን፡፡ በወቅቱ የማዕበል ፈንቴ ዘዋሸራ የቅኔ ዘራፊ አርፎ ነበር፡፡ ቅኔ ዘራፊው የሊቁን ወንበር ወርሶ ስማቸውን ያስጠራል የሚል ተምኔት ነበረን፡፡ በአጭር ተቀጨ፡፡ አልቅሰን ቀበርነው፡፡ ከልቅሶው መልስ መምህሬ በፈረስ ፈጥነው ወደ ሞጣ ተመለሱ፡፡ እኔ በእግሬ ሳዘግም ከመሼ በከንቱ ጋር መንገድ ላይ ተገናኘን፡፡ መሼ በከንቱ ሀገር ለሀገር በመንከራተት ይታወቃሉ፡፡ አንድ አሮጌ አኽያም ነበራቸው፡፡ በአኽያው ዘወር ዘወር እያሉ የማይሰበስቡት ጥራጥሬ አልነበረም፡፡ ገብስ፣ ጓያ፣ አተር፣ ሽንብራ ከባላጋር አውድማ በእንተ ማርያም እያሉ ለአብነት ተማሪዎች በመዝከር ይታወቃሉ፡፡ የቆሎ ተማሪ ሲሞት ደግሞ አልቅሰው ይቀብራሉ፡፡ ያን ቀንም ከልቅሶ መልስ አበያ ከሚባል ሸለቆ ተገናኘን፡፡ ከልቅሶው መልስ የሁለታችንም መንገድ ወደሞጣ ነበር፡፡ ከዚያ በፊት ከሞጣ ቅኔ ቤት ያውቁኛል፡፡ አውቃቸዋለሁ፡፡ መሼ በከንቱ በአኽያ፣ እኔ በእግሬ ወደሞጣ ስንወርድ ምድር



Scanned with CamScanner

የትዝታ ፈገግታ ፈገግ ብለው ወደአሁኑ ግልብ ዘመን ተመለሱ::

"ታች አምና ወደመኻል ሀገር ብቅ ብዬ ነበር:: የዛሬዎችን ዘመናይ የአብነት ሊቆች ድክመት አይቼ ስቈአለሁ:: የመሼ በከንቱን ያኽል እንኳን ገበሬ አስደንግጥ ጥበብ ከእጃቸው ላይ የለም::" አሉ ዐራት ዐይናው ቀለሙ የዚህ ዘመን ትውልድ ከቀደምት ክርታቶች ጋር እያነጻጸሩ::

ታሪኩ ፈገግ ብሎ "ይህ ትውልድ ወዴት ያመጣዋል:: ከዚህ ዘመን ካህናትኮ በሙት በሙቱ መሼ በከንቱ ይሻላሉ::" ሲል አገዛቸው::

"አዎን! እውነት ነው! የዚህ ዘመን አዋቂዎች ጥይት የሚገዝት ጥበብ ቀርቶ ፍቱን መስተፋቀር እንኳ የላቸውም። አሁን አሁንስ ከፊል የስምንተኛው ሺህ ሊቃውንት ነጠላ ዶሮ እየሆኑብኝ ተቸግሬአለሁ:: ሊቅነታቸው ሲደፈር እንደሕጻን ልጅ እጃቸውን በራሳቸው ላይ ጭነው ያለቅሳሉ:: ባላገር ሚስታቸውን ቀምቶ ክህነታቸውን ያስፈረሳቸውን ውትልፍ ቀሳውስት ሳይቀር አይቼ አዝኛለሁ:: ሚስቱን ከባላገር ያላዳነ ካህን ለቤተ መቅደሱ ዘብ እቆማለሁ ቢለኝ የዘመኑ ሐሳዊ እሱ እንደሆነ ጥርጥር የለውም:: ሰባኪዎችስ ቢሆኑ? በቃንጆ ሴት ከመታጀብ በቀር ምን ቁም ነገር አላቸው? የመሼ





በከንቱን ያኽል ገበሬ አስደግጥ ጥበብ እንኳን መቼ ከእጃቸው ላይ ይገኛል:: ሌላው ቀርቶ የሚጠቅመውን የአበውን ጥበብ መቼ ወረሱት ብላችሁ ነው? እኔ እንጃ ብዥታ የስፈረባቸው ነው የሚመስለው:: በቃላት እንጂ በጥበብ የታነጹ መስለው አልታዩኝም:: ይልቁንም ውኃ የመሰለ መኪና ሲነዱ አይቻለሁ:: የዚህ ዘመን ውድድር ያ ይመስለኛል:: ቆርቆሮ መግፋት ብረት መግራት:: ብለው መሼ በከንቱን አስታወሱ:: መሼ በከንቱ ክርታታ ቢጤ ሰው ነበሩ:: በየሀገሩ እየዞሩ ከባለገሩ ሽንብራ በእንተ ማርያም እያሉ ሲያጠራቅሙ ይከርማሉ:: ወደል አኽያም ነበራቸው:: ሽንብራ ለምነው ስልቻቸው ሲመላ በአኽያቸው እየጫኑ ወደ ቅኔ ቤት ይሄዳሉ:: ቅኔ ቤት ገብተው ያን ሽንብራ ለቅኔ ተማሪዎች አካፋፍለው ቀለብ ሰጥተዋቸው "እናንተ ተግታችሁ ተማሩ:: እኔ በእንተ ማርያም እያልሁ ቀለብ እችላችኋለሁ" ብለው አሁንም ሽንብራ ልመና በየሀገሩ ይንከራተታሉ:: ራሳቸው ግን በሰው ፊት እንጀራ ሲቀምሱ ሽንብራ ሲቆረጥሙ ታይተው አያውቁም:: በዚህም ከሰው ከሰው ሲለዩ መና በነፋስ አምጥተው ይመገባሉ እየተባሉ ይታማሉ::

ዐራት ዐይናው መሼ በከንቱን ሲያስታውሱ ደቂቃዎች ቢያልፉም ወደጀመሩት ወግ ተመለሱ::"የድሮ የቅኔ ተማሪዎችኮ የወግ አልነበሩም:: በጥበብም ሆነ በቀለም አንቱ



Scanned with CamScanner

የተባሉ ሊቆች ነበሩ። ሕይወታቸው በክፉም በደግም የሚነካ ከቅኔአቸው እኩል ጥይት የማያስመታ ፍቱን ፍቱን ጥበብ ስለ ነበራቸው ነው። እንደ ዛሬው የአፍ ዘመን ሳይመጣ የአብነት ሊቆች ከእግረ ተማሪዎች ልዩ ነበሩ። አሁን ግን መናፍቁን ከሊቁ እግረ ተማሪውን ከእውነተኛው ተማሪ መለየት ያዳግታል። የነጮች ውስብስብ ሴራ ይህንን የመሰለ ክሹፍ ኢትዮጵያዊነት ፈጥሮብናል። እንደወርቅ የጠራውን ኢትዮጵያዊነት ቀምቶናል።" ብለው ወደባላገሩ ታሪክ ተመለሱ።

"ባላገሩ ደሞሽ ጥይቱን ከጠብመንጃው ጎድጉዶ በተደጋጋሚ ለመተኮስ ምላጭ ቢረግጥ ቃታ ቢስብ ዲሞትፈሩ ቂብ ቂብ እያለ ዝም አለ። እንደበቱ እየተሣሣረ 'እናንተ አስማተኞች! እናንተማ አስማታሞች ናችሁ! አዎን! ምትሐት ስትመትቱ የሰው አንደበት ቀርቶ አፈ-ሙዝ አይቀራችሁ! ምትሐታሞች! መሣሪያዬን በአስማት ቆለፋችሁት' ከቆላው በሽታ አምጥታችሁ ልጆቼን ልታስፈጁብኝ? ወይኔ! የበላይ አሽከር! ወይኔ አጅሬ! እያለ ሲርበተበት ቤቱን ለቅቀን ወደዱር ሄድን፡ ፡ ከቤቱ አለፍ እንዳልን አፈ-ሙዙን ገዝተን ሰውዬውን ፈታነው። በዚህ ጊዜ ነበር የመኻል ሀገሩን ጎብስተ መና የተጠቀምነው።" ብለው ወደጎብስተ መና ጥበብ ተመለሱ።





ታሪኩና ገሞራው ጆሯቸውን አቆንድሸው እየሰሙ ነው። ዐራት ዐይናውም ማብራራት ቀጠሉ።

"ከሰውዬው ቤት ጥቂት አለፍ ብላ አንዲት ለምለም ዋርካ ነበረች። ከዱሩ መካከል የበቀለች ዘርፋፋ ዋርካ ናት። የቅጠሏ ልምላሜ እንደሰንበት መክፈልት ቅመሱኝ ቅመሱኝ የሚል ዋርካ ነበረች። ለእግዜር እንግድነት መረጥናት። ከዋርካዋ ሥር ቁጭ እንዳልን ውሽንፍሩ ቀጠለ። የቆምንባት ምድር ጭቃ በጭቃ ሆነች። እንደፈረደብን ውቅያኖሱን ተሸከምነው። የመሸ በከንቱ አኽያ ጆርባው አዘበዘበ። ከጆርባው ላይ በረዶ ተቆለለ። ገመዱን ከአፉ አውልቀን ጭነቱን አውርደን ተቀመጥንበት። በረዶው ከራሳችን ላይ ገገረ። የብርዱ ነገር ለወግም አይመችም ነበር። ጥርሴ ርስ በራሱ እስኪጋጭ ድረስ አንዘፈዘፈኝ። ወዲያው የባሕር ዳር ወባ ተቀሰቀሰችብኝ፡ ፡ በዚህ መኻል ግን ከዚህ መጣ ያላልሁት ረሐብ ውስጤን ቦረቦረኝ። ከረሐቡ ጋር የወባውን ሕማም መቋቋም ሲያቅተኝ ተስፋ ቆረጥሁ። መሼ በከንቱ ብዙ ወጡ ወረዱ። ከወባው በላይ ረሐቡ እንደጎዳኝ ስነግራቸው ነበር ወደጎብስተ መና ጥበብ ዘው ብለው የገቡት።" ብለው በዐይናቸው እንባ መላ። መሼ በከንቱ በዐይናቸው ውል አሉባቸው። ከቅኔ ትምህርት ጎን ለጎን ከተለያዩ ሊቆች ጋር በፍሥሓ ያሳለፉትን ዘመን በትዝታ አምጥተው በልባቸው ጻፉት። እነሆ ያ ዘመን የቅኔ

ዘመን ነበር። ያ ዘመን የጥበብ ዘመን ነበር። ያ ዘመን የመፈላሰፍ ዘመን ነበር። ያ ዘመን ጃንሆይ በጃማይካ ሰማይ ሥር ዝናም ያዘነሙበት ብርቅ ድንቅ ዘመን ነበር። ያ ዘመን ኢትዮጵያ በሊቆች የደመቀችበት የአፍሪካ እናት የሆነችበት ዘመን ነበር። በዚያ ዘመን ሀገራችን ጫፍ እስከጫፍ የተፈጥሮ አረንጓዴ የለበሰችበት የልምላሜ ዘመን ነበር። ያ ዘመን የጥበብ ጸደይ የፈካበት ዘመን ነበር" እነገሞራው ሲደመሙ በትርክቱ ገፉበት።

"ምድር በማዕበል ስትመታ የእኔ ሆድ በረሐብ ተመታ። ውስጤ ነደደ። ከበረዶው ይልቅ በረሐቡ ደቀቅሁ። መሼ በከንቱ እንደዋዛ 'ወስፋትህ ተንጫጫ አይደል?' ሲሉኝ ምን ጥያቄ አለው? ከወባውና ከብርዱ ይልቅ ረሐቡ አደከመኝ አልኋቸው። ለ"መሼ በከንቱ" ምኑ ይቸግራችዋል? እንጀራ በእጃቸው ጥበብ በደጃቸው ነው! ቅጽበት ሳይቆዩ ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው ከእኔ ጥቂት አለፍ ብለው 'የዛሬ ያልሆነ ጥበብ ለመቼ ነው? ከፈለገ ፈጣሪ ሲያል ይወርውረኝ። እንጦርጦስ ይጣለኝ። በጥበቡ እጠቀምበታለሁ። አንድ ሊቅ በረሐብ ተይዞ በወባ ተነድፎ በረሐብ ሲሞት ቆሜ አላይም' እያሉ ሲቀበጣጥሩ ቆይተው ከዚህ መጣ ከዚህ ተገኘ ያልተባለ መና ከፊት ለፊት መጥቶ ተንዘኀዘ። ከነፋስ ድምፅ በቀር የሰው ኮቴ አልነበረም። የእንጀራው ውፍረት ልሙጥ





ድንጋይ ይመስላል። መሼ በከንቱ "እስኪ ይህንን ድንጋይ ወዲህ በለው? በክፉ ቀን እኔም ተዋነይ ነኝ። የችግር ቀን እኔም ሙሴ ነኝ። ልብሴን ከሰሌን ቅጠል እሰፋለሁ። ምግቤን ከድንጋይ ላይ እጋግራለሁ" ሲሉ በውኔ ቁጭ ብዬ እየሰማሁ የታዘዝሁትን ፈጸምሁ። መሶበ ወርቁ በጎብስተ መና ተሞልቷል። ከፊት ለፊታችን በተዘጠረው ጎርፍ እጃችንን ታጥበን ረጅም ጸሎት አደርገን መመገብ ጀመርን።" ብለው ከተረኩ በኋላ "ያን ጊዜ የሰዉሩ ዓለም መና በነፋስ የመጣ መስሎኝ ደስታው የልብ ምቴን ጸጥ አድርጎት ነበር። በኋላ እየቆየሁ መናው የሞት መግቻ አለመሆኑን እየተረዳሁ መጣሁ። ያን ያመንሁት መሼ በከንቱ ያረፉ ቀን ነበር። ያ መና የሰዉሩ ዓለም መና ሆኖ ቢሆን መሼ በከንቱ በሕይወት ይኖሩ ነበር ስል ከመኻል ሀገር ያየሁትን ምሥጢር ውብ ቢሆንም ከሰዉሩ ዓለም ካለው ጋር ቅንጣት ተመሳሳይነት እንደሌለው ተረድቼ ሰዉሩን ዓለም ማሠሤን ገፋሁበት። ተንከራትቼ ተንከራትቼ ከእውነታው የጥበብ ዓለም ላይ ዱቅ አልሁ።" ብለው ዝም ሲሉ

"ጥፍጥናው ግን ተመሳሳይ ነው?" አለ ታሪኩ።

"የሰዉሩ ዓለም መና ጥፍጥና ከመሼ በከንቱ መና የተለየ ነው። የሰዉሩ ዓለም መና መዓዛው በራሱ መድኃኒት ነው።



Scanned with CamScanner

"ወጥ ወጡን ተረባርበን ተመግበን ደረቅ ደረቁ ሲቀር ለመሼ በከንቱ አኽያ ሰጠነው:: ያንን ሰፊድ ግንጭሉን እያመላገደ ሸመሸመው:: መሶበ ወርቁም አልቀረው:: ቀረጠፈው:: ወዲያኑ አንድ መወድስ ዘርፌ ሳልጨርስ እንቅልፍ በዐይኔ ተኳሰ:: በሕይወቴ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለእንግድነት ከሄድሁ ዕለቱን እንቅልፍ ወስዶኝ አያውቅም ነበር:: ይህ ከተፈጥሮዬ አንዱ ክፍል ነው:: ከአንድ ቤት ወደሌላ ቤት ስሄድ እንቅልፍ በዐይኔ ሳይኳል ያድራል:: ይህን ግም ዐመል ታቅፌ እኖራለሁ:: ዛሬም ድረስ ከቤቴ ወጥቼ ከሌላ ቤት ከተኛሁ በዚያች ሌሊት እንቅልፍ በዐይኔ አይዞርም:: እንቅልፍ የሚይዘኝ ከሁለት ቀን በኋላ ቤቱን እንደቤቴ ስለምወደው ነው:: በቀር ግም አመል አለብኝ:: ያን ቀን ግን መናው ከባድ እንቅልፍ አመጣብኝ:: እስከ ንጋቱ ሁለት ሰዓት ተኛሁ:: በኋላ መሼ በከንቱን ተከትዬ ጥበባቸውን እያደነቅሁ ወደቅኔ ቤቴ ተመለስሁ:: ከዓመት በኋላ ከርኩስ ወይስ ከቅዱስ መንፈስ ነው ትኩስ እንጀራ የሚመጣ የሚለውን ለማረጋገጥ መሼን በከንቱን አጥብቄ ጠየቅኋቸው:: ወደማኅበረ ሥላሴ ገዳም ይዘውኝ ወረዱ::" ካሉ በኋላ ቀና ብለው በሰማይ የተዘረዘሩ ከርታታ ኮከቦችን ተመለከቱ:: ሌሊቱ እንደገፋ፣ ሰዓት እንዳለፈ ከርታታ ኮከቦች አበሰሯቸው:: ምሽት ላይ ከምዕራብ





ተነሥተው አሁን መኻል ሰማይ ደርሰዋል:: ዐራት ዐይናው ከፊታቸው ፊቅ እንዳሉ ተሰወሩ:: ሁሉቱ ሲደመሙ አፍታ ቆይተው ተኙ::

## ፴፪

ማኅበረ ሥላሴ ጎንደር

ማለዳ• ሲመጡ ገሞራውና ታሪኩ ከእንቅልፍ ላይ ነበሩ። ተኝተው ስለ መናው ሕልም ላይ ሳሉ ዐራት ዐይናው ቀለሙ ቀሰቀሷቸው። በያዙት ጭራ ቾብ ቾብ ሲያደርጓቸው ከሕልም ተናጠቡ። ጭራቸውን እያወዛወዙ ከፊታቸው ቆመው ነበር። ጭራቸው ከወሎ ሲወጡ አብራቸው የወጣች ነጭ ጭራ ናት። ዓመታትን አብራቸው አሳልፋለች። ሲሰወሩ አብራ ስዉሩን ዓለም ተቀላቅላለች። ዐራት ዐይናው ቀለሙ ተፈሪ የቆላ ዝንቦችን ሲጥ ያደርጉታባል። ብዙ ተሐዋስያን ከንፎቻቸውን ያጡት በዚች ቁንን ጭራ ነው። ከዘራና ጭራቸው ሥምረት ፈጥረዋል። "የኔታ የመናውን ታሪክ ይጨርሱልን? ከርኩስ መንፈስ ወይስ ከቅዱስ መልአክ የተገኘ መና ነው? ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ከሄዳችሁ በኋላ አመጣጡ ከወዴት እንደሆነ ተረዳችሁ? እሱን ይጨርሱልን። ታሪኩ ልባችን እንዳንጠለጠለው ነው የቀረው?" አለ ታሪኩ።

"ከቅዱስ ነገር እንደሚገኝ ጭምጭታ አግኝተናል። እርግጠኛ ለመሆን ግን ሰፊ ምርምር ይጠይቅ ነበር። መሼ





በከንቱ አረፉ። እኔም ትቼው ወደዚህ ዓለም መጣሁ። ወዲህ መጥቼ መልአከ-ሞትን መግታት ቻልሁ።

እግዜር ይመስገን። ቦሩ ሥላሴ ብሆን ኑሮ እንደ አካልዬ ይህን ቀለም ይጀው መቃብር እወርድ ነበር። መናው ከሞት ገላገለኝ።" ካሉ በኋላ ወደ ኋላ በሐሳብ ተመልሰው የገጠማቸውን ታሪክ ተረጋግተው አብራሩት።

"ወደ ቅዱሱ ገዳም መሄዳችን ለሁለት ነገር ነበር። ትኩሱ እንጀራ ከቅዱስና ከርኩስ መንፈስ መምጣቱን ለማረጋገጥ ሄደን ሞፈር ቤት ከሚባለው የገዳሙ የእርሻ ክፍል ተጠጋን። እንደምታውቁት በገዳም ያለሥራ መዋል ማደር ክልክል ነው። በዚያ መሠረት እኔ አኽያ ጠባቂ ሆኜ ተመደብሁ። መሼ በከንቱ ረድእ ሆኑ። ቋሚ ሥራ አልተሰጣቸውም። በገዳም የረድእ ሥራው ቋሚ አይደለም። ወጪ ወራጅ ሥራ ነው። ሰይጣን ድል በሚነሣበት ቅዱስ ገዳም ቁጭ ብለን የመናውን መምጫ ለማወቅ ሞከርን።" ሲሉ ቀጠሉ።

"የምንለውን ብለን በመጀመሪያ ከቅዱሱ ገዳም መኮሬታ እንዲመጣ አዘዝን። መኮሬታ የገዳም ምግብ ነው። ትኩሱ መኮሬታ መጣ። የሰይጣን ጥበብ አለመሆኑን መገመት ጀመርን። እንዲያውም ጥበበ-ተዋነይ ሊሆን ይችላል

እስከማለት ደርሰን እንደነበር ትዝ ይለኛል::" አሉ ዐሬት ዐይናው ገዳም ለገዳም የተንከራተቱበትን እድሜ ወደኋላ ተመልሰው እየተረኩ::

"ከገዳሙ ቢመጣስ "ቅዱስ" ሲሆን እንደሚችል በምን አረጋገጣችሁ? የአስማት ኃይል ከገዳም ገብቶ መኮሬታውን በርኩስ መንፈስ ጭኖ ቢያመጣውስ?" ገሞራው ጫን አድርጎ ጠየቃቸው::

"ለዚህ አይደል ቅዱስ የሆነውን ገዳም የመረጥነው? ለምን ታቃጥላለህ? አታጋልጠኝኮ ነው ማለት!" ብለው ገሞራውን በወጉ ገስጸው ቀጠሉ::

"ምእመናን እጅ በመንሣት፣ ኢአማንያን በታሪክ እንደሚያውቁት ማኅበረ ሥላሴ ቅዱስ ገዳም ነው:: ታላቁ አባታችን ዐምደ ሥላሴ ይህንን ገዳም የመሠረቱት እልም ባለው በረኃ ውስጥ ሲሆን በአካባቢው የሴት ድምፅ ቀርቶ እንስት ወፍ ዘምራበት አታውቅም:: ርኩስ መንፈስም መግባት አይችልም:: እርግጥ ነው! ረቂቁ ጋኔን ገብቶ ገዳማውያንን ሊፈትናቸው ይችላል:: የተባረከውን መኮሬታ ግን ማምጣት ቀርቶ የመንካት ኃይል የለውም:: የገዳሙን መኮሬታ ወደእኛ ማምጣት ይቅርና ከግዝት በር አይደርስም:: ጸሎቱ ይቆራርጠዋል:: ከዚሁ ጎን ለጎን ግን ከገድላቸው





ብዛት የተነሣ ሰይጣንን ተገልጦ የሚያዩ አበው አሉበት:: እነሀ ናቸው እንዷል መጋቢና ዋና መጋቢ እየሆኑ መኮሬታ የሚጋግሩት:: መኮሬታውን ጋግረው ለአበው አስባርከው ለገዳማውያኑ ያቀርባሉ:: እነሀ ባሉበት ቅዱስ ስፍራ ሰይጣን ከገዳሙ መኮሬታ ሊነካ አይችልም ብለን ነው:: በዚያ ላይ ሰይጣን ከግዝት በር አልፎ ሕርመት ወደሚባለው ከመኮሬታ በቀር እንጀራ ወደማይገባበት ክፍል ማለፍ እንደማይችል እኔም ሆነ መሼ በከንቱ እናውቃለን::

እናም ከዕለታት አንድ ቀን ከገዳሙ ጫፍ ቁጭ እንዳልን መሼ በከንቱ የገዳሙ መኮሬታ እንዲመጣልን አዘዙ:: ጥቂት ቆይቶ ነፋስ ሽው ሽው ማለት ጀመረ:: ቅጽበት አልቆየም:: የገዳሙ መኮሬታ መጥቶ ከፊታችን ቁጭ አለ:: ዘወር ዘወር ስል የሰው ድምፅ የለም:: ምን አልባት በስዋሬ ሰው አምጥቶት ከሆነ ብዬ እኔም ስዋሬዬን ተጠቀምሁ:: ወፍ የለም:: የገዳሙ መኮሬታ መጥቶ ከፊት ለፊታችን ቁጭ እንዳለ ስመ እግዚአብሔር ጠርተን ባርከን ተመገብነው::" ሲሉ ቁጭ አድርገው ተርከው

"እንግዲህ ያን ቀን የገዳሙ መኮሬታ እንዲመጣልን የፈለግነው ከገዳሙ መንጠቅ ፈልገን ሳይሆን የጥበቡን ቅዱስነት ለማረጋገጥ ነበር:: በነፋስ የሚያመጣው መንፈስ

ርኩስ ከሆነ ገዳም ገብቶ መከራታውን ማምጣት አይችልም። ትኩስ እንጀራ እየጫነ የሚያመጣው ቅዱስ መንፈስ ከሆነ ግን ያመጣዋል። የጨበጥነው ጥበብም ቅዱስ መሆን አለበት ብለን አምነን ሞክርነው። መከራታው መጣ። በልተን ከፈጸምን በኋላ መሼ በከንቱ አንድ ወር በረድእነት ገዳሙን አገልግለው ንሥሓ ተቀብለው አገልግለው ወደመኻል ሀገር ተመለሱ። እኔ በፈቃዴ ገዳሙን እየረዳሁ ለሦስት ዓመታት ቆይቻለሁ። ከመከራቸውም ሱታፌ ነበረኝ። አኽያ ጥበቃ ተመድቤ ለሦስት ዓመታት ያኽል ጠብቄአለሁ። ከሊቀ ረድኡ ጋርም አዝመራ ሰብስቤአለሁ። አካሄዴ ይህንኑ ለማረጋገጥ ቢሆንም መዋሸቱ ግን አልቀረም። መጋቢው እንድመነኩስ ሲጠይቁኝ አመጣጤ ለቆብ አይደለም። አጽመ አበውን ተሳልሜ ከአበው ተባርኬ ወደ ሀገሬ ለመመለስ ነው ስል ውሸቴን ደረገምሁት። ተቀብለው አኽያ ጥበቃ መደቡኝ። ከኢትዮጵያ የቅኔ ሊቆች መኻል በአኽያ ጥበቃ የተመደበው የመጀመሪያው ሰው እኔ ሳልሆን እቀራለሁ? ሁ..ሁ! በእርግጥ በዋልድባ ብዙ ሊቆች ሊቅነታቸውን ደብቀው አኽያ ለመጫን ይመደቡ እንደነበር ሰምቻለሁ። ለእኔ ግን የተለየየ የሥራ ምርጫ ቀርቦልኝ ነበር። ከቀረቡልኝ አማራጭ ሥራዎች በመጀመሪያ ከመጋቢው አፍ የወጣው የአኽያው ጥበቃ ነገር ነበር። ለጥቆ የጠላ ብቅል መጠበቅ፤ ለጥቆ





ወደአዝመራው ማሳ ወርዶ ወፍ ጥበቃ ቀርበውልኝ ነበር። ብቅል መጠበቁ ብዙ አልሳበኝም። ደብረ ቢዘን ሳለሁ ተማርሬበታለሁ።" አሉ ቀለሙ ተፈሪ።

"እሬ ጉድ ነው! ደብረ ቢዘንም ነበሩ?" አለ ገሞራው አሁንም ለጥበብ ሲሉ የተንከራተቱ መስሎት።

"አዎን! ከርታታ ነበርሁ። አቡሻህር የቀጸልሁት ደብረ ቢዘን ነው። አቡሻህር እየተማርሁ ስጦ እጠብቅ ነበር። ወፎች ደግሞ ጥሩ አልነበሩም። ዝማሬአቸው መልካም ቢሆንም የተመሰጠ ጊዜ አይሰጡም። አቡሻህር •እየቀመርሁ ስጦ ስጠብቅ ከተመሰጠ እያባነኑኝ እቸገር ነበር። በማኅበረ ሥላሴ ግን አኽያ መጠበቅ ቀለለኝ። አኽዮች ብዙ አያስቸግሩም። ሣር ነጭተው ውኃ ተጎንጭተው ከርሳቸው አታሞ ሲያክል ከጥላ ሥር ያርፋሉ። በእርግጥ በግ ቢኖር ኑሮ የበግ ጥበቃ ይለፈኝ የማይባል ሥራ ነበር። ወፍና ፍየል ጥበቃ ግን ለተመሰጠ አይሆንም። ሁለቱም ፋታ አይሠጡም። ይህንን አውጥቼ አውርጄ አኽያ ጠባቂ ተመደብሁ። በዚህ ጊዜ ነው እንግዲህ የገዳማውያንን ተጋድሎ የተረዳሁት።" ብለው ፋታ ሲወስዱ

"ገድላቸውን እንዴት ይገልጹታል?" አለ ታሪኩ እርእያ አድርጎ ሊወስደው።

"በገዳሙ ውስጥ ላሉ አበው ተጋድሏቸው ጭንቅ ነው:: የመጀመሪያው ገድል የተፈጥሮ ውኃ አለመኖር ነው:: ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ውኃ ከከርሠ ምድር ለማውጣት ጀማምረው ነበር:: በጣሊያን ወረራ ጊዜ ተደረመሰ:: ጃንሆይም የአቅማቸውን ወጥተው ወርደው ነበር:: እግዜር የፈቀደላቸው አይመስልም:: ገዳሙን ከውኃ ጥም መታደግ አልቻሉም:: አበው ግን ውኃ ጥሙን ለገዳሙ የተሰጠ በረከት አድርገው በደስታ ተቀብለውት ይኖራሉ:: ገዳማውያኑ የሚኖሩት ውኃ ተቆንነው ነው:: መቆነን ማለት ጠብታ ውኃ ከቅል ተቆርጦ በተሠራ ፋጋ መታደል ወይም መከፋፈል ማለት ነው:: ይህን ተከትሎ በገዳሙ ያሉ አባቶች ውኃ ይጠጣሉ ማለት አይቻልም:: ምላሳቸውን እንኳን የሚያረጥቡት በገዛ ላባቸው ነው:: በረኃው ሲወብቅ ሰውነታቸው ላብ በላብ ይሆናል:: ምላሳቸውን ወደሰውነታቸው እየላኩ ያረጥባሉ:: ከጉሮሯቸው ባይወርድም በውኃ ጥም የከረረ ምላሳቸው ጠብታ ያገኛል:: ላባቸው ጨው ጨው ከማለት በቀር የሚፈጥረው ችግር የለውም:: ያው ወታደሮች በጦር ሜዳ ሲጨንቃቸው ሽንታቸውን እንደሚጠጡት ቆጠሩት:: አንዳች ልዩነት የለውም:: ከጠብታው ውኃ በቀር ያው የፈረደበት የታቆረ ውኃ ደሞ አለ:: የጉሮሯቸው ማርጠቢያ እሱ ነው:: ክረምት ክረምት





በስሱም ቢሆን ዝናም ይዘንባል:: እንደአቅማቸው ውኃ ያቆራሉ:: በጋ ሲመጣ ወበቅ ሲጀምር ጠብታ ውኃ መከፋፈል ይጀምራሉ:: በመጋቢው በኩል እንደጥሬ የጠብታ ውኃ መቆነን ይጀምራሉ:: የፈለገ ጉሮሮውን ያረጥባል:: ያልፈለገ መነኩሴ ከጠብታውም ራሱን ከልክሎ በውኃ ጥም ተሰቃይቶ ያልፋል:: የያዙት ያው ምናኔ ስለሆነ አንድ መነኩሴ ጠብታ ውኃ ሳይቀምስ ቢሞት ደስታው ነው:: እንዲጠጣ የሚያስገድደው አካል የለም:: ድርሻው ግን አይቀርበትም:: ያለአድልዎ ጠብታ ውኃ ይሰጠዋል:: አንዳንዶች ከወፎች ጋር ተከፍለው ይጠጡታል:: ገሚሶች ከሦስት ቀን ለአንድ ቀን ብቻ እየጠጡ ለወፎች ያጠጧቸዋል:: ተጋድሎው እስከዚህ ድረስ ነው::" የረሱትን እያስታወሱ ብዙ ገለገሉ:: ሁለቱ ሊቆች ግን በዚህ ገድልም ተመስጠዋል:: ከሕይወት ፊደል ጽናትና ብርታትን እየቀጸሉ ነው::

"በገዳሙ ከነበረኝ ቆይታ የማልረሳው ነገር ቢኖር የውኃና የእንጀራ ናፍቆት ነበር:: እንጀራ ከሞፈር ቤት በቀር ወደዋናው ገዳም አይገባም:: ውኃ የለም::" ካሉ በኋላ በገዳሙ የነበሩበትን ጊዜ አስታወሱት:: መልካም የአኽያ እረኛ ነበሩ:: ወደል ወደል አኽያ ጠብቀዋል:: አለሌ አኽያም ሞክተዋል:: ሲሞክቱ የአኽያ እንትን አውጥተው ጥለዋል:: ትዕቢተኛውን አለሌ በለበቅ ገርፈዋል:: አለሌ አኽያ ተሞክቶ እንኳ ትዕቢት

እንደሚተናነቀው የተረዱት በዚሁ ገዳም ነው:: ጊዜም ትዕቢተኛውን የቅኔ ተማሪ በእለሴ አኸያ መስለው ቅኔ ዘርፈውበታል:: እማርኛና ግእዝ ቀመስ ቅኔ ነበር:: እለሴ አኸያ ተሞክቶ እንኳን ትዕቢቱን አይተውም! ሌላው ደግሞ ሆዱ አይጣል ነው:: በልቶ በልቶ ፋንድያው በወሉ ግጥም ይላል:: ያን መንተት አበሳ ነው የሚል ሐሳብ ነበረው:: ቀለሙ ተፈሪ ይህንን ቅኔ ለማስታምስ በዝምታ ተውጠው ከአምስት ደቂቃ በላይ ቆዩ:: ነገር ግን ትዝ ሳይላቸው ቀረ:: ዘመኑ ረጅም ዘመን ስለሆነ መወድሱን ከሥር ጀምረው ሊያመጡት አልቻሉም:: ዘመኑ ርቆ ተሰወራቸው:: እርግጥ ነው በቅኔ ሊቆች ዘንድ ያለፈውን መወድስ አለማስታወስ የዝንጋኤ ምልክት አይደለም:: የባለቅኔዎች ወግ ነው:: ባለቅኔዎች አዳዲስ መወድስ ይፈጥራሉ እንጂ ከሠላሳ ዓመት በፊት የዘረፉትን ቅኔ እንደቅኔ አይቆጥሩትም:: ባለቅኔዎች እንጂ ዘፋኞች አይደሉምና! ዘፋኖች ባንዲት ነጠላ ዜማ ትንፋሻቸው ለዘለዓለም ሲንቆረቆር ይኖራል:: አንዲት ነጠላ ዘፈን ከዘፈኑ በኋላ ብቻ መድረክ ያገኙ እንጂ እድሜ ልካቸውን ያቀነቅኗታል:: ዘፈናቸው መቶ ዓመታት ቀርቶ መቶ ኢዮቤልዩ ድረስ ይዘፈናል:: ትንፋሻቸው ተቀርፆ ለትውልድ ይተላለፋል:: ለሀገር ይተርፋል:: ባንድ ጎኑ በጎ ነገር ቢሆንም የእስትንፋሳቸውን ስርቅርቅነት እንጂ





የእእምሯቸውን ሊቅነት ግን አያሳይም:: ባለቅኔዎች ግን ከቀንቀኞች ይለያሉ:: ምርጥ ደራሲዎች ናቸው:: በሕይወት እስካሉ ድረስ አዳዲስ ቅኔ ከመፍጠር አሮጌውን ዓለም በአዲስ መልክ ከመቃኘት የሚያግዳቸው አሮጌ ዘመን የለም:: በቀላሉ እንደዘፋኞች ድምፅ፣ እእምሮቸው አያረጅም:: እውቀታቸው አይጃጅም:: ከሠላሳ ዓመት በፊት የሙዚቃ ዜማ ያንቆረቆሩ የሙዚቃ ሊቆች ድምፃቸው እንዳማረ ዐርባ ዓመት አይደፍኑም:: እርጅና ይሰልባቸዋል:: ትርፉ ትዝታ ብቻ ነው: : ከሰባ ዓመት በፊት ቅኔ ይዘርፉ የነበሩ ሊቆች ግን አሁንም ከመወድሱ ገበታ አልተገለሉም:: .መወድሱ በውስጣቸው ይፈላል:: የእእምሮ ሠረገላቸው ይገነፍላል:: በውስጣቸው የቅኔ ነበልባል ይንበለበላል:: እእምሯቸው እፍ ቢሉት እሳተ-ነበልባል ነው:: ዐራት ዐይናው ያለፈውን ዘመን በተመስጦ ሊቃኙ ትንሽ ጊዜ ቢወስዱም ፍሬ ነገሩን ግን አልረሱትም:: ወደ ጀመሩት ታሪክ ተመለሱ::

ከገዳሙ ቆይታዬ የገድላቸው ጽናት ጽኑእ ሰው አድርጎኛል:: ገዳማውኑ ተርበው ረሐብ አስተምረውኛል:: ሰው ፊደል ብቻ ሳይሆን ረሐብንም መማር እንዳለበት የተማርሁበት በዚሁ ገዳም ነው:: እንጀራ ቀርቶ መኮሬታው በሰዓቱ አይገኝም:: ጾም ኖረም አልኖረም ከዐሥር ሰዓት በፊት መኮሬታ አይሰጥም:: እርም ነው:: ይህ ሊደንቃችሁ አይገባም::

"መጀመሪያ መኮሮታው በነፋስ ሲመጣ ጥበበ ተዋነይ መስሎኝ በደስታ ስከር ብዬ ሰክሬ ነበር። ከዚያ በሰው እጅ መምጣት አለመምጣቱን ለመረጋገጥ ሞከርሁ። በአካባቢው የሰው ኮቴ አልነበረም። ኋላ ከመኮሬታው ቀመስሁ። በጥበቡ ባምንም በአፌ እየዞረ መዋጥ ተሳነኝ። እየቆየሁ ግን ቀስ በቀስ ለመድሁት። ለሦስት ዓመታት ያኽል ቆየሁ። በዚህ ጊዜ ምን ውል ይለኝ እንደ ነበር ታውቃላችሁ? ማኅበረ ሥላሴ ሳለሁ?" ሲሉ ትንታኔውን ገቱ።

"ቅኔ ሊሆን ይችላል። አኽያ እየጠበቁ ከቅኔ ቤት ስለራቁ ከቅኔ በቀር ሌላ ምን ትዝ ሊልዎት ይችላል? መወድስ መሆን አለበት።" አለ ታሪኩ።

"እሄሄ ወይ ቅኔ መናፈቅ እያ! ውል እያለ ያስቸገረኝ የጣና ውኃ ነበር። የባሕር ዳር ሕዝብ ጣና ቆሻሻ ነው እያለ በነጮች መድኃኒት የታከመ ውኃ ሲጠጣ ይኖራል። በምን አይነት መድኃኒት እንደሚታከም ግን ከባለሙያዎች በቀር አያውቀውም። ነጮችን አምኖ ውኃ አክሞ ይጎነጫል። ከማኅበረ ሥላሴ ገዳም ስትሆን ግን የታከመ ውኃም ሆነ የምንጭ ውኃ አይናፍቅም። የምንጭ ውኃ ቀድቼ ጠጥቼ ጥሜ የሚረካም አይመስልም። ውል የሚለው እንደሰፊው ሰማይ የተሰጣው የጣና ውኃ ብቻ ነው። ተምኔቱም ወደጣና





ተመልሼ ከውኃው ጠጥቼ ገላዬን በቀዝቃዛው ተለቃልቄ መሞት ነበር።" ሲሉ ገሞራውና ታሪኩ ከንፈራቸውን መጠጡ።

"ትዝ ይለኛል! አኽያ ስጠብቅ አንድ ቀን ጠብታ ውኃ ተሰጠኝ። ስመለከተው ትላትል አፍርቷል። እሳት አንድጄ ውኃውን አፍልቼ ልጠጣ ስዘጋጅ መጋቢው ወደበዓቴ መጡ። ሁኔታዬን አስተውለው ውኃ አፍልቶ መጠጣት ክልክል ነው። የአበው ቃል ይፈርሳል ሲሉ ሥርዐተ አበውን ገለጹልኝ። ከዚያ በፊት ይህንን ሰምቼ አላወቅም ነበር። ምን ማድረግ ይቻላል! "ለእመ ሖረከ ብሒረ ባዕድ ኩን ከማሆሙ" የሚለውን ቃል ቀድሜ አውቀዋለሁ። ሕንጻ መነኮሳት በሚባለው መጽሐፍ ይገኛል። ይህንን ቃል ከመሻር ብዬ እስከ ትሉ ተጋጠምሁት። ከጉሮሮ ከወረደ ሁሉም ባዕድ ነው ስል ተጽናናሁ።" ብለው ሲጨርሱ

"መናውን ግን ቅዱስ እንጂ ርኩስ መንፈስ እንዳላመጣው ተረዳችሁ አይደል?" አለ ገሞራው።

"ለጊዜው መስሎኝ ነበር። የተዋነይ ጥበብም መስሎን ነበር። እንደሚታወቀው በገዳሙ ውስጥ መኮሬታው ተባርኮ ሳይቆረስ ከቤተ እግዚአብሔር አይወጣም። ይህ ሊሆን የቻለው ደግሞ በቤተ እግዚአብሔር ውስጥ ያሉ የአበው በረከት



Scanned with CamScanner

"ዴንሳ እመኒ ወተወከሊ ይልማና።

እብን በከመ ልማዱ ፡እስመ ኮነ መና።" የሚለውን ቅኔ ታውቁታላችሁ?" አሉ ዐራት ዐይናው

"እኔ ሰምቸው አውቃለሁ።" አለ ታሪኩ

"ይህ ቅኔ ከቅኔነቱ ይልቅ የመሼ በከንቱን ምሥጢር ይጠቀማል። መወድሱ በቀላል ቅኔ የተሰነደው ግእዝ ቋንቋ እማያውቁ ጭምር በቀላሉ እንዲረዱት ነው። መርምሩት። ከሳምንት በኋላ እመለሳለሁ። ካመጣችሁት በሶና ዶቅማ ፍሬ በደንብ ተመገቡ። ማሩም ይኸው። ከሳምንት በፊት አልመጣም።" ብለው ተሰናብተዋቸው ተነሡ። ጥቂት ራመድ ራመድ ካሉ በኋላ በሀገር የሉም። ያው እንደ ልማዳቸው ተሰውረው ይሆናል.።





# ፴፮

ቅኔዋ

ቀን መጽሐፍ ሲያነቡ ውለው ምሽት ላይ ጥቂት ዘወር ዘወር አሉ። ከዚያም ወደዶቅማው ተመልሰው ያወጉ ጀመር።

"ይህች ቅኔ ብሉያን መዋዕል ሊቆችም ያውቋታል ማለት ነው? እኔ ከወሬ ወሬ ቅኔዋን ሰምቻት ነበር። ምርጥ መወድስ ናት። ኩልከሙ መወድስ ትባላለች። ባለቅኔው ረጅሙ መወድስ ለተራው ሕዝብ ቀርቶ ለካህናትም ከባድ ስለሆነ ሊቆች ይችን አጭር መወድስ ለጥበቡ እንደመረጧት ጥርጥር የለውም። ያ ባይሆን ይህንን የመሰለ ረጅም ሐሳብ ይዘው ረጅም መወድስ መዘረፍ ይችሉ ነበር። አጭር መወድስ ያደረጉት ጥበበ ተዋነይን በቀላሉ ከሰው ጆሮ ለማድረስ ፈልገው ይመስለኛል። ዐራት ዐይናው ከመራት ተነሥተው ይችን ቅኔ መርምሯት አላሉም። መናው ከድንጋይ የሚገኝ ይመስለኛል።" ሲል ገሞራው በቅኔዋ በኩል ተፈላሰፈ።

"አንተከ ልዩ ነህ። ከማንም ሊቅ ትለያለህ። አንገትህን ስትደፋ ምንም የምታውቅ አትመስልም። መልክአ ፊደል የቀጠረ የሚመስል ገጽ እንኳ የለህም። ሰዎች በዋዛ

ገሞራው ፊገግ ሲል ያ አሻቦ የመሰለ ጥርሱ በሚዳ ላይ ተሰጣ። ሰመመን ዐይኖቹ ተስመነመኑ። ከዚያም የቅኔው መብረቅ የተባለበትንም ወግ ማስተባበል ጀመረ።

"መቼም የቅኔ ቤትን ኩሸት አንተም ታውቀዋለህ።"

"ብትክክል" ታሪኩ ተስማማ።

"እንደ ልባችን እንኳሽ ነበር። እንደልባችን መወድስ እንዘርፍ ነበር። አልፎ አልፎማ መምህራችንን ጭምር የመናቅ አባዜ ጭምርኮ ነበረን። ይህንን አንተም ታስታውሰዋለህ። ቅኔ ቤት ሳለን ዓለምን እንቀልድባት ነበር። ለእኔም መብረቁ የሚለው ስም የተፈጠረው በቀልድ በቀልድ ነበር። ቅኔ ቤት ሳለሁ ነበልባል የሚል የተማሪ ስም ሰማሁ። በዚህ ስገረም ማዕበል የሚባል ስም ደግሞ ተደገመ። ማን ከማን ያንሣል ብዬ እኔም መብረቁ በሉኝ ብዬ አወጀሁ። ባንድ ሰሞን ራሴን መብረቁ እያልሁ እጠራ ጀመር። በዚያ ላይ መብረቁ ማለት ማዕበሉ እንደ ማለት ነው። ምንም ከባድ ነገር አይደለም። እናልህ ስሜን መብረቁ ብለው እንዲጠሩኝ ለጓደኞቼ ነገርኋቸው። ተማሪዎች መብረቁ! መብረቁ! እያሉ ሲጠሩኝ ሰምቶ አንድ ጓደኛዬ በቅንዐት ነደደ። ስሙ ነዌ ነበር። እልም ያለ ንፉግ ነው። ስስቱ ደግሞ አይጣል ነው። የራሱን ኮቸሮ መንደር ቀብሮ ከእኔ ጋር ነበር የሚመገበው። ጏላ ላይ መብረቁ የሚለው ስሜ በቅኔ ቤቱ ተጋኖ ሲጠራ በቅንዐት ጤሰ። በሳምንቱ እሱም ስሙን ከነዌነት ወደ ነጐድጓድ ለወጠ። ነጐድጓድ ተባለ። ያ ከርሣም ተማሪ የቅርብ ጓደኛዬ ነበር። ለምን በዚህ ቅጽል ስም እንደተጠራ ሳጣራ ገሞራው መብረቁ ከተባለ እኔ ደግሞ ነጐድጓዱ ተብዬ መጠራት አለብኝ ብሎ እንደተፋለመኝ ሰማሁ። ማንም ከርሣም ከተፎካከረኝ ምኑን መብረቁ ሆንሁት ብዬ በነዌ ላይ መወድሶችን አዘነብሁበት። እሱም አጻፋውን እመልሳለሁ ብሎ ዘረፋ ገጠመኝ። ዘረፋ የተጋጠምነው ቅዳሜ ከሰዓት ነበር። ጀንበር ተሰናብታ ቤቷ ገብታ የደብሩ ደወል ተደውሎ ለአገልግሎት የመጡ ካህናቱ እስኪገላግሉን ድረስ አመሽንበት። እኔ አያሌ መወድሶችን ስወነጭፍ ነዌ ሁለት መወድሶች እየተኮላተፈ ዘረፈ። እኔ ስዘርፍ የቅኔ ተማሪዎች መብረቁ! መብረቁ! መብረቁ! እያሉ ስሜን በሙገሳ እየጠሩ እያጨበጨቡ አጀቡኝ። አያሌ መወድሶችን አኽጎደጎድሁበት። እሱ ግን ሁለት እንደወረወረ እንደውኃ ወፍጮ "ድ..ቅ..ድ.ቅድቅድቅ" ብሎ በዚያው ጭልጥ አለ። የቅኔ ትንፋሽ አጠረው።" አለ ገሞራው።

"ላንተ ቅኔ ክፍልህ ነው። ሌሎች ሲጠሉት በአንተ ግን ይሠምራል። አንተ ግን ቅኔ ጠላቴ ነው ትላለህ። እኔ ግን የጠላት ባርኮት ስጦታህ እንደሆነ አምናለሁ።" አለ ታሪኩ።

"ሙሉ ዕጣ ፈንታዬ ሌላ እንደሆነ ባውቅም በመወድሱ በኩልም ውስጤ ያምናል:: በእርግጥ ከነዊ ጋር ዘረፋና ዘለፋ በገጠምንበት ሌሊት በሕልሜ ከማዕበል ኢያሱ ጋር አድሬ ነበር:: በነዊ ላይ የቅኔ መዓት አፈስበታለሁ ብዬ ጠብቄ ግን አላውቅም ነበር:: በሕልሜ ከማዕበል ኢያሱ ጋር ስላደርሁ መሰለኝ በመወድሱ ተጠመጠምሁበት:: ነዊ አረፋ ሲዘፍቅ አሳዘነኝ:: እኔ ግን በተደጋጋሚ የዘለፋ መወድስ አወርድበት ነበር:: ስኖር የስድብ ቅኔ የተቀኘሁት ያችን ቀን ብቻ ነው:: ያን ቀን ለሰንበት አገልግሎት የመጡ ካህናት እንደምንም አፋፍሰው ወደጎጆዬ ባያስገቡኝ ኑሮ ተተርትሬ መውደቄ የሚቀር አልነበረም:: ትዝ ይለኛል:: መምህራችንም "ከልፋች!" ከለፈተውኮ እያሉ ጥለውኝ ወደቤታቸው ገቡ:: ነጉድጓድም ቢሆን እንደ አቅሙ በሁለቷ መወድስ ሲወነን ካህናቱ በተሳልቆ ገላግለው ወደ ጎጆው አስገቡት:: በነጋታው የቅኔ ተማሪዎች ጉባኤ ሠርተው ነጉድጓድ በዚህ ስም መጠራት እንደሌለበት ወሰኑ:: ነጉድጓድ ግን ሁላችን ቅኔ ዘረፋውን ያቆምነው በካህናቱ ግልግል እንጂ አሸናፊው አልታወቀም ነበር ብሎ በቅጽል ስሙ መጠራቱን ቀጠለበት:: የቆላ ቁሶች እውነት የቅኔ ዘራፊ መስሏቸው እሱን ነጉድጓድ እኔን መብረቁ እያሉ መጥራት ቀጠሉ:: በስም ካስተካከሉን በመምህርነትም መተካከል ስለመሰለኝ በድጋሜ ጉባኤ አድርጌ





የቅኔ ዘራፊዎችን ሰብስቤ መብረቁን ሻርሁት:: በቀደመ ስሜ በገሞራው ቀጠልሁ:: መብረቁ የሚለው ቅጽል ግን ዛሬ ድረስ በቅኔ ቤት የቅጽል ስሜ እንደሆነ አልፎ አልፎ ይነገራል:: አሁን ስሜ መብረቁ አይደለም ገሞራው ነው::" ካለ በኋላ ገሞራው ቀጠለ::

"እኔም ታሪኩ ታሪኩ ስትባል ሰምቼ በደፈናው ትናፍቀኝ ነበር:: እድለኛ ነኝ:: አብረን ለመኖር በቃን:: ጥበብ አጣመረችን:: ይኸውና አያሌ የጎንደር ታሪኮችን አስረዳኸኝ::" ካለ በኋላ::

"ሌላስ ስለእኔ ምን ይወራል?" አለ ገሞራው ከቅኔ ቤት ከተለየ በኋላ ስለእሱ ምን ምን እንደሚወራ ለማወቅ ፈልጎ::

"ብዙ ብዙ ይወራል:: ቀደም ሲል አብዷል ተብሎ ተወርቶ ነበር:: መልሶ ከሰመ:: ሌላ ጊዜ ደግሞ ሕንድ ሀገር ገብቶ ጥበብ ተምሮ ተመለሰ ተባለ:: ቆይቶ ግን እንደተዋነይ በደመና እየተጫነ ግሪክ ሂዶ ቅኔ መማር ፈልጎ ነበር:: ነገር ግን ተዋነይ ግሪክ ሄዶ ቅኔ እንዳልተማረ በጥናት ሲያረጋግጥ የአንተም ወሬ ደበዘዘ:: ባሕር ዳር ላይ ግን አሁንም ቁሶች እንደጃርት ወስፌ ይፈሩኻል:: ድሮ የባሕር ዳር ቁሶች ሞት ለገሞራው እያሉ ይመኙ እንደነበር እኔም አውቃለሁ:: ባንድ ወቅት ደግሞ ቅኔ ቤት ወጥቶ ጥበብ ፍለጋ ሄደ እየተባለ

በባሕር ዳር ተናፍሷል። በወቅቱ እንደጉድ ተወርቷል። የማዕበል ኢያሱን ጥበብ ለማፈላለግ ከቅኔ ቤት ወጥቶ ሄደ ተብሎ ሲወራ ሰምቼ ሳዝን እኖር ነበር። አንተ ከቅኔ ቤት ወጥተህ ለጥበብ ስትንከራተት ጎንደር ቅኔ ቤት ነበርሁ። የመጀመሪያ ያየሁህም ጎንደር የመጣህ ቀን ነው። ባለቅኔው ገሞራው ይህ ነው ብለው የቅኔ ቤት ጓደኞቼ ሲነግሩኝ ማመን ተሳነኝ። እንደ ኒቆዲሞስ እየተጠራጠርሁ እንደዘካርያስ እየተከራከርሁ ቶሎ አላመንሁም ነበር። ከዚያም በራስህ ላይ እየቀለድህ የዘረፍኸውን ቅኔ ጓዋደኛዬ ነገረኝ። መወድሱን ከሰማሁ በኋላ በአያሌው ማመን ተሳነኝ። ይህንን የመሰለ ፍልስፍና ተሸክሞ ሀገር ለሀገር ምን ያንከራትተዋል? አርፎ አያስተምርም እንዴ? ስል ራሴን ጠየቅሁ።" አለ ታሪኩ ስለገሞራው ክርታታነት በከፊል ሲያወጋ።

"ከዚያስ?" ገሞራው ቀስ ብሎ ጠየቀ።

"ከዚህ ኮስማና ውሽልክ ቢጤ ሰው እንዲህ ያለ ቅኔ አይወጣውም ብዬ ተከራክሬአለሁ። በኋላ ግን ትንሽ ወደልቤ ገባህ። ወደ ጎንደር የምትመላለስበትን ምሥጢር ስሰማ ቀስ በቀስ እያመንሁ መጣሁ።" ሲለው ገሞራው ፈገግ አለ። የአንክሮ ፈገግታ ፈገግ ሲል በገጹ ላይ የምሥራቅ ወጋገን ፈካበት። እንደ ሐምሌ የጨለመ ገጹ ዳምኖ እንደ በጋ ሰማይ





ኩልል አለ። ቀጫጫ ጣቶቹን እያፋተለ ወደውስጡ ጥቂት አሰቦ ወጉን እንዲጨርስለት ተማጠነው። ጓደኛውም ቀጠለ።

"ቀስ በቀስ ያንን ነገር ፍለጋ ነው የሚመላለስ ሲሉኝ አስማተኛ መስለኸኝ ነበር። መፍቀሬ ጥበብ ትሆናለህ ብዬ አልገመትሁም ነበር። በዚያች ሌሊት ጋደም ብዬ አንድ ነገር ልቤን መታው። ሕልም እንዳይመስልህ። አንተ የምትፈልገው ምሥጢር ከአቃቤ ሰዓት አበሞ ሕይወት ጋር እንደሚዛመድ ሳውቅ ስለአቃቤ ሰዓት አበሞ ጠልቄ ሳስብ አደርሁ። በነጋው ስለ አቃቤ ሰዓት አበሞ የሕይወት ታሪክ የሚያጠነጥን መጽሐፍ ፈለግሁ። ምንም ላገኝ አልቻልሁ። የጽሑፍ ማስረጃ ሳጣ በጎንደር ውስጥ በታሪክ አዋቂነታቸው ወደሚደነቁት ሊቅ ገሠገስሁ። በዚያ ሰሞን እንደልማዳቸው አልነበሩም። ስለ ክርታታ ኮከቦች የሚቀምረውን መጽሐፍ ለማንበብ ደንቢያ ወርደው ነበር። ደጅ መጥናቴን አዘወተርሁ። አንድ ቀን ከሰማይ የወረደ መልአክ መስለው ተመለሱ። ነገር ከሥሩ ነውና ከሥር ጀምሬ ስለአቃቤ ሰዓት አበሞ ጠየቅኋቸው። መጀመሪያ አቃቤ ሰዓት አበሞ የሀገር ሊቅ እንጂ የአስማት ሰው እንዳልነበሩ አሳመኑኝ። አንተ የምትፈልገው ጥበብ ሳይሆን ከቀመር ጋር የተሳሰረ ምሥጢር እንደሆነ መቋሚያቸውን እየጣሉ ጭራቸውን እየገረፉ አረጋገጡልኝ። ከእሳቸው መልስ ወደ ቅኔ ቤት



Scanned with CamScanner

አልተመለስሁም፡፡ ወደ አንተ መጣሁ፡፡ አንተም በፈገግታ ተቀበልኸኝ፡፡ ማታ ተያይዘን ወደብልኮ ሰፈር አቀናን፡፡ በወቅቱ በብዙ ነገር ጠርጥሬህ ነበር፡፡ ከአጠገብህ ቁጭ ብዬ ስመለከትህ አንገት ደፊ ቅኔ ዘራፊ ነገር ነህ፡፡ ሴት ቀና ብለህ አታይም፡፡ ከማኅበረ ሥላሴ ወደጎንደር የመጣ መናኝ መሰልኸኝ፡፡ በተለይ ይህንን ከራሳቸው ከሴቶች አንደበት ተረድቻለሁ፡፡ ሴቶች "ዐይን አፋር ነው" ይሉኻል፡፡ አንድ ቀን ብልኮ ሰፈር ያን ሲቅ መፈለግ የሄድን ቀን አንዲት ልጅ በፍቅር ወድቃልህ ነበር፡፡ ብትቅበጠበጥ ዐይን ዐይንህን ብታይ ወዲያ ወዲህ እያለች በምልክት መንገር ብትፈልግ ቅንጣት ያኽል ሳይገባህ ቀረ፡፡ የአብርሃም በግ መሆንህን የተረዳችው ልጅ መጥታ "የአብርሃም በግ ሙክት ነው?" አለችኝ፡፡ ደንግጬ ወደአንተ ቀና ስል አንተ የተቆጣውን የዐጤ ቴዎድሮስን ፎቶ እየተመለከትህ ለንቦጭኽን ጥለኻል፡፡ ወደልጅቷ ዘወር ስል "ምርጥ ጓደኛ አለህ፡፡ ወደፊት ግን ብልኮ ሰፈር አታምጣው፡፡ ወደ ዋልድባ ገዳም ውሰደው፡፡" ብላ እየሳቀች ወጥታ ሄደች፡፡ ከዚያ ተመኝታህ እንዳልተሳካላት ገባኝ፡፡ ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ ሰብእናህን ወደድሁት፡፡ ሊቅነትህን አከበርሁት፡፡ በነጋታው ወደ እኛ ቤት ለምሳ ሄድን፡፡ እናቴ ገና አሁን ጥሩ ጓደኛ አገኘህ፡፡ ዐይናፋር ነው፡፡ ጭምት ነው፡፡ ስትል ሹክ አለችኝ፡፡ እኅቴ ግን በፍቅር ዐይን





ተመልክታህ እንደ ነበር እናቴ ነገራኛለች፡፡ የሴትን ምሥጢር ሴት ናት ቀድማ የምታውቀው መሰለኝ፡፡ አንተ ግን ያው የአብርሃም በግ ሆነህ ቁጭ ብለኻል፡፡ ከዚች ቀን በኋላ በተደጋጋሚ ብልኮ ሰፈር ስንሄድ ባንተ ነበር የምንሰሳቀው፡፡ የአብርሃም በግ ቀንዱ የከረከረ ጸጉሩ ያረረ ነው፡፡ ከአቅመ አዳም አልፎታል፡፡ ጥፍሩ ገርድፏል፡፡ እግሩ ጀልፏል እያልን በዚህ በገረጀፈው ዱልዱም ጥፍርህ እንስቅ ነበር፡፡" ሲል እየቀለደ ሳይሞት ምሉእ የሕይወት ታሪኩን ነገረው፡፡ ከዚያ ሁለቱም ወደ ገሞራው የእግር ጥፍር ተመለከቱ፡፡

በማጭድ ካልታጨደ በቀር በምላጭ የሚቆረጥ ለስላሳ ጥፍር የለውም፡፡ ሁለቱም ተያይዘው ሳቁ፡፡ በተለይ ገሞራው ጓደኛው ያነሳውን ነገር በሐሳብ እያመጣ ተንከትክቶ ሲስቅ በዐይኑ እንባ ተዘረገፈ፡፡ ሲስቅ ለእናቱ ቀብር የሚሆን እንባ ያጎርፋል፡፡ ሲቆጣ ለንቦጨን ይጥላል፡፡ ሲተኛ ደግሞ አፉን ከፍቶ ነው፡፡ ይህን ጨርሰው ወደቅኔዋ ምሥጢር ሲመለሱ

"ዴንሳ እመኒ ወተወከሲ ይልማና፡፡

እብን በከመ ልማዱ እስመ ኮነ መና፡፡" የሚለውን ቅኔ ግን ከዚህ በፊት በትክክል ታውቀው ነበር?" አለ ገሞራው፡፡

"አዎን! አውቀዋለሁ"

"ምን ማለት ነው?" ገሞራው ሰፍ ብሎ ጠየቀው

"ጼንሳ ተረጅልኝ እመኚ ይልማና፡፡

ድቡልቡሉ ድንጋይ መና ሁኗልና፡፡"

ማለት ይመስለኛል፡፡" አለ ታሪኩ፡፡ ትርጉሙ ቀላል ነው፡፡ ግእዙን ወደአማርኛ ተርጉምልኝ አላልሁም፡፡ ምሥጢሩን ነው የጠየቅሁት?" አለ ገሞራው፡፡

"እሱን አላውቀውም፡፡ መወድሱ የመናውን ምሥጢር ሳይገልጥ አይቀርም" አለ ታሪኩ

"እንዴት ስትል?"

ታሪኩ እጁን ከደበሎው አውጥቶ ትረካውን ቀጠለ

"በገደምዳሜው የሰማሁት ጎንደር ደብረ ብርሃን ቅኔ ቤት ሳለሁ ነበር፡፡ በዘጠናዎች ውስጥ አንድ የቅኔ ዘራፊ የጎንደር የቅኔ ዘራፊዎችን በቅኔ ዘረፋ ለመግጠም ወደ ጎንደር መጥቶ ነበር፡፡ የጎንደር አብያተ-መንግሥታትን ጎብኝቶ የአብነት ተማሪ ቤቶችን ማሠሥ ቀጠለ፡፡ ከጉዛራ ቤተ መንግሥት ከወጎኒ አምባ ማርያም እንዲሁም ከኢትዮጵያዊ ፈላስፋ ከዘርዐ ያዕቆብ መንደር እንፍራዝንና ከታች ፍርቃ በርን አዳርሶ ጎንደር ሲደርስ ቀጥታ ወደደብረ ብርሃን መጣ፡፡ ቅኔ





ቤቱ ሙቀ ቅኔ ዘረፋው ደምቆ ነበር፡፡ ከባለ ቅኔው ከክፍለ ዮሐንስ ቅኔ ቤት ሲገባ መምህራችን በፍቅር ተቀበሉት፡፡ በሣልስቱ መወድስ ዘረፋ ሲጀምር የእኛን መምህር በቅኔ ዘረፋ የሚወዳደሩኝ የቅኔ ዘራፊዎች ይስጡኝ አለ፡፡ ያ ሁላ ወፌ ሰማይ ተማሪ እንዲሰበሰብ የቅኔ ቤቱ ደወል ተደወለ፡፡ በወቅቱ እኛ የቅኔ ዘራፊዎች ከላይ በአንገረብ አፋፍና ከታች ከሸጡ ሆነን መጽሐፍ እያጠናን ነበር፡፡ እኔ ወደቅኔ ቤቱ በፍጥነት እንደተፈለግሁ ተማሪ ተላከ፡፡ ስደርስ ከግምጃ ቤት፣ ከፊት አቦ፣ ከቁስቋም፣ ከሌሎችም የጎንደር አብያተ ክርስቲያናት ያሉ በርካታ የአብነት ተማሪዎች ደብረ ብርሃን ቅኔ ቤትን አጥለቅልቀዋታል፡፡ የተማሪውን መጥለቅለቅ ተመልክተው አንድ በምርኩዝ እየተደገፉ ጎበጥ ብለው ባጠገባችን የሚያልፉ ሽማግሌ በዐጤ ፋሲል ጊዜ ፈረስ ጉግስ ለማየት የጎንደር ሕዝብ እንዲህ ግልብጥ ብሎ ይወጣ ነበር ይባላል፡፡ ዛሬ ደግሞ ምን ተገኝቶ ነው ይህ ሁላ ወፌ ሰማይ ተማሪ ተገልብጦ የወጣው ብለው የልጅነት ትዝታቸውን ተናግረው በምርኩዛቸው እየተደገፉ አለፉ፡፡ ያ ተማሪ ከክፍለ ዮሐንስ ቅኔ ቤት ካላችሁት የቅኔ ዘራፊዎች ጀምሮ ከተለያዩ የጎንደር አድባራት የመጣችሁ ቅኔ ዘራፊዎች ተመራርጣችሁ ቅኔ ዘረፋ ግጠሙኝ ብሎን እርፍ አለ፡፡ ከአፍታ በኋላ በጎንደር ሕዝብ ፊት ቅኔ-ዘረፋ ገጠምን፡፡

ከዐርባ ዐራቱ የጎንደር አድባራት የተሰበሰብን የቅኔ ዘራፆች ለቅኔ ዘረፋ ስንሰለፍ ከቁስቋም አንድ ጥርስ ሸራፋ ቅኔ ዘራፊ ተመረጠ። ከአቡን-ቤት ገብርኤል ሴት ቅኔ ዘራፊ ተላከች። ከቁመቷ ጀምሮ በቅኔዋ መለሎ ነበረች። መልኳ የሶሪት ላባ ይመስላል። የጎንደር ልጆች ቀይ ዳማ ቁንጅና ጎልቶ ይታይባታል። መልኳ የቀይ ዳማ፣ ቁመቷ እንደሸንበቆ መለሎ ነው። ሎጋዎች ከወገቧ አይደርሱም። በቅኔዋም ሆነ በምሥጢር አመጣጧ ቅመም ነበረች። ከደብረ ብርሃን ቅኔ ቤት እኔ ተመረጥሁ። ስለክፍለ ዮሐንስ ክብር ሲባል የመጀመሪያው መወድስ ለእኔ ተሰጠ። ደበሎዬን አደግድጌ ያንን መወድስ ተጠመጠምሁበት። እንደ ክፍለ ዮሐንስ በባዶ እግሬ እየሄድሁ መወድሱን አንጐደጎድሁት። በመጀመሪያው የቅኔ ጊዜዬ እንደሌላው ቀን እልፍ አእላፍ መወድስ መዝረፍ አልፈለግሁም። ምሥጢራቸው ሰማየ-ሰማያት፣ ትርጓሜቸው ፀባዖት የደረሱ ሰባት መወድሶችን ተዘለጥሁባቸው። ታዳሚዎች ጨምር! ጨምር! ታሪኩ ጨምር! ሲሉኝ በሰባቶቹ የጎንደር ተራሮች ልክ ሰባት መወድስ ከዘረፍሁ በቂዬ ነው ብዬ ዝም አልሁ። የጎንደር ቁስቋሙ ሸረፎ ዐራት መወድስ ወረወረ። ባለቅኔዋ ራሷን ተከንናባ በሴቶች በኩል ተሰልፋ በመወድሷ ምጥቀት በቅኔዋ ብስለት አቧራ አሰበሰችን። ሁላችንንም የሚያስንቅ መወድስ ዘረፈች። ከደብረ-ብርሃን እስከ ራስ ግንብ መወድስ እየዘረፈች ጎንደርን የቅኔ ከተማ አደረገቻት። የጎንደር ሕዝብ እንደጎዳር ንብ ተገልብጦ ወጣ። ራስ ግንብን በመጎብኘት ላይ የነበሩ ፈረንጆች ባለቅኔዋን እየተከተሉ ፎቶ ግራፍ ያነሱ ጀመር። ሴቷ ባለቅኔ መወድሱን አውርዳው አውርዳው ሲበቃት የእኔ መወድስ በድጋሜ አገረሸ። በድጋሜ ቅኔ መዝረፍ እንደጀመርሁ ደበሎዬ ከትከሻዬ ወርዳ ከእግሬ ሥር ተጠቀለለች። ያች ሴት ባለቅኔ ነጠላዋን ከሩቅ ሆና ወረወረችልኝ። ነጠላዋን በወገቤ አደግድጌ በመወድስ ዘረፋው ገፋሁበት። ቀስ ቀስ እያልሁ ቅኔ እየዘረፍሁ ሳላውቀው ከራስ ግንብ እስከዣንተከል ዋርካ ወረድሁ። ዣንተከል ስደርስ የቅኔ መምህሬ ከፊት ለፊቱ ዋርካው ሥር ተራ ልብስ ለብሰው አጭር ከዘራቸውን ይዘው ፈገግ እያሉ ተቀበሉኝ። ከዚያም 'ተዉ! ተዉ! ተው ይበቃል። አሁን ይህ ሁላ ሕዝብ ይከተላል እንጂ ግእዝ አይሰማም። ይህንን የመሰለ መወድስ በሜዳ መዝራት አግባብ አይደለም ብለው ከለከሉኝ። ከጎጃም የመጣው የቅኔ ዘራፊም በመወድሴ ሲደመም ቆይቶ ሲዘርፍ አፈፍ ብሎ ሲነሣ የደብረ ብርሃኑ ሊቅ በፍቅር ተቃወሙ። እሱንም እንደእኔው አስተዉት። ሕዝቡ ወደቤቱ ተበተነ። መሸት ሲል የደብረ ብርሃኑን የቅኔ መምህር አጅበን ወደቅኔ ቤታችን መንገድ ጀመርን። ከሳምንት በኋላ

ዴንሳ እመኒ ወተወከሲ ይልማና።

እብን በከመ ልማዱ እስመ ኮና።" የሚለውን ቅኔ ጠየቀኝ። እንደማላውቀው ነገርሁት። ይህን ቅኔ የዘረፉት ሊቅ አሁን በሕይወት የሉም። ቅኔው ግን የቀለሙን ቅኔ ይመስላል ሲል ተነፈሰ። እግረ መንገዱንም የቀለሙን ጥበብ የሚችሉ በጎጃም ሊኖሩ ይችላሉ ብሎ ወደጎጃም ይዞኝ መጣ። በሳምንቱ ተያይዘን በገመድ በር ዐባይን ተሻግረን ጎጃም ገባን። በእግረ መንገዱ ፍቅረ ቢጽ መሠረትን። በኢትዮጵያ ያሉ ቅኔ ቤቶችን ለመፈተሽ ተስማማን። ከእኔ ይልቅ ለእሱ ስሙኒ ሳንቲም ነበረው። በስሙኒዋ ጌጠኛ ጫማ ገዛልኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ ጫማ በሙጀሌ እግሬ የሰካሁት ያን ቀን ነበር። በኋላ ሞጣ ቅኔ ቤት ገባን። ሞጣ ሳለን

ዴንሳ እመኒ ወተወከሲ ይልማና።

እብን በከመ ልማዱ እስመ ኮነ መና።" የሚለውን በድጋሜ አነሣው። ምን ማለት ነው ስለው

"ዴንሳ ተረጅልኝ እመኝ ይልማና።

ድቡልቡሉ ድንጋይ መና ሁኗልና።" ማለት ነው አለኝ። ምሥጢሩን ስጠይቀው ቀለሙ ይዞት ተቀብሯል። ሂድና ቀለሙን ከተቀበረበት ቀስቅሰው እያለ እንባውን ሲያፈስ





ከረመ። በዓመቱ ጥሎኝ ጠፋ። ይኸው ትናንት የኔታ ቅኔዋን ሲያመጧት እንባ ተናነቀኝ። ይችን ቅኔ ከእኔ በቀር ሌላ ሰው እንደማያውቃት እገምታለሁ። ቅኔዋም በቅኔ መጽሐፍ አልተጣፈችም። ከሌላ ሰው እንደበትም ሰምቻት አላውቅም። የቅኔዋ ምሥጢር ኀቡእ ነው። ጥበብ ነክ መወድሶች በአብዛኛው ጊዜ በጉባኤ አይነገሩም። ለተመረጠ ተማሪ ብቻ በሹክሹታ ይነገራሉ። የድሮ የቅኔ ሊቆች ጥበባቸውን በቅኔ ይገልጡና ለመረጡት ብቻ ያስተምሩት ነበር። ይህ ቅኔም የኀብስተ መናን ምሥጢር የያዘ ይመስለኛል። የቅኔ ዘራፊም እኒህ ሊቅ ይመስሉኛል።" አለ ታሪኩ።

"ድንጋዩ ዳቦ ሲሆን? አይመስለኝም።" ብሎ ገሞራው በረጅሙ ተነፈሰ።

ከዚያም "የቅኔ ዘረፋው ወግ ግን መስጦኛል። ይህን መሰል የዘረፋ ፈተና ግን እኔንም ገጥሞኝ ያውቃል። አንተን የፈተነው ሊቅ እኔንም ፈትኖኝ ይሆን?" አለ ገሞራው እሱም ዋሸራ ሳለ የገጠመው የቅኔ ዘረፋ ፈተና ትዝ ብሎት።

"በመቼ ዓመተ ምሕረት ነበር?"

"በዐሥራ ዘጠኝ ዘጠና ስድስት ዓመተ ምሕረት ይመስለኛል።" አለ ታሪኩ።



Scanned with CamScanner

"በትክክል! እኔም በትኔ ዘረፋ የተፈተንሁት በዚህ ዓመት ምሕረት ነበር። ትዝ ይለኛል። የዋሸራ ሰማይ በቅኔ ሲታረስ እኔም የቅኔ ማረሻዬን ሞርጄ ቀርቤ ነበር። ምን እኔ ብቻ! የእንኮበሩ ወልደ ሐና፣ የጎጃሙ ሠረገላ፣ የዋድላው ባቱኤል፣ የጎንደሩ ዘፍሱልሱፍም በዋሸራ ቅኔ ቤት ነበሩ። ሁሉም በቅኔ መምህርነት ተመርቀዋል። ዐራቱ የቅኔ ዘራፊዎች ከተለያየ ቅኔ ቤት የተማሩ ሲሆን ቅኔ ስቧቸው ጥበብ ጠርታቸው ዋሸራ ተሰበሰቡ። በዚህ ወቅት አንድ የቅኔ ሊቅ ወደዋሸራ መጣ። አንተ እንዳልኸው የዋሸራ ዘራፊዎች ከየጎጇችሁ ብቅ ብቅ በሉና ቅኔ ዘረፋ እንግጠም ሲል የቅኔ ቤቱን ደወል ደወለ። ዐራታችን ወጥተን ገጠምነው። ዘረፋ እንደጀመርን የዋሸራው ሊቅ የማዕበል ፈንቴን ስም እየጠራችሁ አንዳንድ መወድስ ብቻ ዝረፉ። መወድስ የሚለካው በረቂቅነቱ እንጂ በብዛት አይደለም። ለዛሬው አንድ መወድስ ይበቃል ብለው ባንድ መወድስ ብቻ ገደቡን። ጎጃሜው ሠረገላ ግን የለም! የለም! ባይሆን ሦስት ሦስት መወድስ ይሰጠን አለ። ባቱኤል ዘዋድላ ሦስት ብቻ በቂ አይደለም! እኔ መዝረፍ ከጀመርሁ ከሰባቱ የወሎ ሊቆች የወረስሁት አብነት ያስቸግረኛል። ሰባት መወድስ ካልዘረፍሁ ራሴ እንደታመመ ነው የሚውለው። ለእኔ ዐሥር መወድሶች ይፈቀድልኝ። በተከታታይ እንደበረዶ ላፍላቸው። እንደተልባ ላንጣጣቸው። ከዚያ በፊት ግን ፍቱን





መድኃኒቴ መቀስቀስ አለበት።" ብሎ ራሱን በኩርኩም ኳ ኳ ኳ ሲያደርገው የሰባቱ የቅኔ ድድቆች አብነት ከመቅጽበት ገነፈለበት። ዐይኑ ተጎሰገለ። ከናፈሩን እየነከሰ ልብሱን እያስተካከለ ቅኔ መዝረፍ ሲጀምር የዋሸራ ሕዝብ ግልብጥ ብሎ ወጣ። ቁራ ገደል በድምፁ ተናወጠ። የመወድሱ መነሻ ሐሳብ አሁንም ትዝ ይለኛል። የተለመደ ግጥም ነበር።" አለ ገሞራው በፈንታው።

"ምን ነበር የተለመደው?" አለ ታሪኩ

"እናትና አባትሽ አይወዱም እንግዳ።

ላሚኝና ልሄድ በመዝጊያው ቀዳዳ" በሚል የፍቅር ሐሳብ ላይ ተመስርቶ ነበር የዘረፈው። መወድሱ የዋሸራን ልጃ ገረዶች ስሜት ድጋሜ ቀሰቀሰ። ግጥሙ ድሮ በማዕበል ፈንቴ ዘመን ለዋሸራ ልጆች የተደረሰ የፍቅር ግጥም ነበር። በማዕበል ፈንቴ ዘመን በፍቅር ላበደች ቆንጆ የቅኔ ዘራፊ የገጠመው ግጥም ነው ይባላል። ይህ ግጥም የተገጠመላት ልጃ ገረድ ያን ደመ ግቡ የቅኔ ዘራፊ ያፈቀረች ሰሞን እናትና አባቷ ተቆጡ። የዘራፊውና የልጇ ፍቅር በእናትና በአባት ቁጣ ሲገታ የቅኔ ዘራፊው ዝም አላለም።

እናትና አባትሽ አይወዱም እንግዳ።

ሳሚኝና ልሂድ በመዝጊያው ቀዳዳ፡፡" ሲል አዜመላት፡፡ ዛሬ ላይ ይህ ዘፈን የሕዝብ ዜማ እስከመሆን ደርሷል፡፡ በዋሸራ ግን ለአንዲት ቆንጆ እንደተዘፈነ ይነገራል፡፡ በፊት አድሙ ዘወለጋ ከዚህ ሐሳብ ተነሥቶ ደብረ ማርቆስ ላይ በማዕበል ፈንቴ መስተፋቅር የሚያጠነጥን መወድስ በግእዝ ቋንቋ ዘርፎ እንደነበር ይተረካል፡፡ በእኔ ዘመን ደግሞ የዋድላው ባለቅኔ ደግሞታል" አለ ገሞራው፡፡

"በማዕበል ፈንቴ ላይ የሚያጠነጥን ነው ስትል ምን ማለት ነው?" አለ ታሪኩ፡፡

"ሀገር ያወጋውን አንተ አልሰማሁም ልትል ነው እንዴ? ማዕበል ፈንቴኮ የተፈተነ መስተፋቅር ጭምር ነበራቸው፡፡ ይህንን ድፍን የዋሸራ ሕዝብ ያውቀዋል፡፡ አድሙ ቅኔውን የፈጠረው የማዕበልን የፍቅር መድኃኒት ተመርኩዞ እግረ መንገዱን ቅኔውን ለሕዝብ ቀለል አድርጎ ገልጦታል፡፡ አዩህ የድሮ ቅኔ ለሕዝብ ብዙ አይገባም ነበር፡፡ ሊቅ ለሊቅ ብቻ ነበር፡፡ ሊቁ ሲቀኝ ሊቁ ይሰማዋል፡፡ ከሕዝብ ጆሮ ግን በትክክል ደርሶ አያውቅም፡፡ አድሙ ዘወለጋ ግን ቀለል አድርጎ ወደሕዝብ ጆሮ ለማድረስ ፈልጎ





እናትና አባትሽ አይወዱም እንግዳ፤

ሳሚኝና ልሂድ በመዝጊያው ቀዳዳ፡፡"

ሲል አመጣው፡፡ የደብረ ማርቆስ ልጃገረዶች አፋቸውን ከፍተው እየሰሙ ነበር፡፡" አለ ገሞራው፡፡ ከዚያም ያለፈውን ጊዜ ተመልሶ በትዝታ ቃኘው፡፡

"ዘረፋ የገጠምንበት ቀኑ ቅዳሜ ነበር፡፡ በዚህ ቅዱስ ቀን ያ ከርታታ ተማሪ የዋሸራን ቅኔ ዘራፊዎች ሊፈትን ወደዋሸራ ብቅ አለ፡፡ ወጥተን በቅኔ ገጠምነው፡፡ መወድሱን ስንጀምር የዋሸራ ሕዝብ ከገበያ መልስ በቅኔ ቤቱ ዙሪያ ተረገረገ፡፡ በዚች ዕለት የዋሸራ ማርያም ሕዝብ ማዕበል ፈንቴ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቷል እስኪል ድረስ ቅኔ ተዘርፏል፡፡ የዋሸራ ሕዝብ በጠፋ በስንት ዘመኑ መወድስ ተመልሶ ዋሸራ ገባ እየተባባሉ ተጠቃቅሰዋል፡፡ በጊዜው የዋሸራው መምህርም ግራ ተጋብተው ነበር" ገሞራው እንደአቅሙ ትዝታ መናገር ጀመረ፡፡ ገና ብላቴና ቢሆንም አያሌ ነገሮችን ቀስሟል፡፡ ለቅኔም ሀገር ለሀገር ተንከራትቷል፡፡ እሱም እንደአቅሙ ከርታታ ኮከብ ነው፡፡

"ምን ግራ አጋባቸው?" አለ ታሪኩ



Scanned with CamScanner

"ግራ ያገባቸው የእኛ መወድስ ነበር፡፡ ዘፍልሱፍ የጎንደርን የቅኔ መንገድ ይዞ ከዋሸራው ሊቅ ፊት ለቅኔ ዘረፋ ከተሰለፈ በኋላ ብስል ብስል ተማሪዎች ሲረዱት ተሰለፉ፡፡ ሠረገላ ተጨማሪ ዘራፊዎች በቅኔ ዘረፋ እንዲያጅቡት አዘዘ፡፡ ባቱኤል ለብቻዬ አሸንፋለሁ ብሎ ስላመነ ማንንም አልፈለገም፡፡ በቅኔ ዘረፋ የተዋጣለት ሊቅ ነው፡፡ ያለምንም ተራዳኢ ቅኔ ዘረፋ ገጥሞ የማሸነፍ ሙሉ አቅም ነበረው፡፡ ወልደ ሐና ከሸዋ አንኮበር እስከ ጎጃም አጅበውት የመጡ የቅኔ ዘራፊዎችን በተጠባባቂነት አስቀምጦ ነበር፡፡"

ገሞራው ከትዝታ መልስ ቀስ በቀስ እያስታወሰ መተረኩን ቀጠለ፡፡

"ባቱኤል ይህን የሕዝብ ዘፈን ወደ ግእዝ ለውጦ ራሱን በእንግዳ የማዕበል ፈንቴን ጥበብ በቆንጆ ልጅ መስሎ መወድሱን ሲያወርደው የዋሸራ ሕዝብ በሳቅ ፈረሰ፡፡ ባቱኤል ግን በላብ ተጠምቆ ይወቃው ጀመር፡፡ ባቱኤል እንደፈጸመ ዘፍልሱፍ ተተካ፡፡ ገና ሲጀምር 'የኔታ! እኔ ከዐሥር ሙሉ ቤት በቀር አፌን አልከፍተውም፡፡ ዐሥር ሙሉ ቤት ሳልዘርፍ ከዚች ቦታ ንቅንቅ አልልም፡፡ እንደባቱኤል ሰባት መወድስ ብቻ ዘርፌ ቅኔ ዘረፍሁ ማለት አልፈልግም፡፡ በጎንደር ያለው የቅኔ አዘራረፍ ከጎጃም፣ ከሸዋ፣ ከትግራይ፣





ከዋድላ፣ ከደብረቢዘን፣ ከአክሱም፣ የቅኔ አዘራረፍ ልዩ ነው፡፡ በጉባኤ ቃና ከጀመርሁ በጉባኤ ቃና ብቻ አበቃለሁ፡፡ ቁጥሩ ግን ከዐሥር በላይ መሆን አለበት፡፡ በመወድስ ከጀመርሁ በመወድስ እጨርሳለሁ፡፡ መወድሴ ግን ከኀምሳ ዝቅ ከሠላሳ ብቅ ማለት አለበት፡፡ በቀር ለሁለት ለሦስት መወድስ ብዬ አፌን አልከፍትም ሲል አወጀ፡፡ የአንኮበሩ ወልደ-ሐና ደግሞ ሌላ ሐሳብ ጎተተ፡፡ በአንኮበር ሊቆች ልማድ የእኔ መወድሶቼ መቆጠር የለባቸውም፡፡ የቻልሁትን ያኽል እዘርፋለሁ፡፡ እኔ እንዳበቃሁ እኒህ ከአንኮበር ድረስ አጅበውኝ የመጡ የቅኔ ተማሪዎች የእኔን ያኽል መወድስ ይዘርፋሉ፡፡ ከዚያም የቅኔው ፍጻሜ ይሆናል፡፡ ብዙ አላስችግርም' ሲል ሊቁ ግራ ተጋቡ፡፡ አመጣጣችሁ የእኔን ማዕበልነት ለመፈተሽ ነው? ወይስ በእውነት ቀለም ለመጠየቅ? ሲሉ ተነፈሱ፡፡ የለም የለም መወድስ ለመዘራረፍ ተፎካክረን ነው አልናቸው፡፡ ያ የዋሸራን የቅኔ ዘራፊዎች ሊፈትን የመጣው ሊቅ ግን ሁሉንም እኔ ብቻዬን እዘርራቸዋለሁ ሲል መለሰላቸው፡፡ ሜዳውም ፈረሱም ይኸው ብለው በቅኔው እንድንሞካከር ፈቀዱልን፡፡ የዋሸራ አቧራ እስኪጤስ አጤስነው፡፡ ባቱኤል እናትና አባትሽ አይወዱም እንግዳን ወደ ግእዝ ቋንቋ ለውጦ ዋዜማና መወድስ እንደዘረፈ ዘፍልሱፍ ቀጠለ፡፡ ምን ያኽል መወድስ እንዳወረደ አሁን ላይ ትዝ አይለኝም፡፡ ብቻ ሀገር

ጠቦት ነበር፡፡ ሠረገላስ ቢሆን ማን ችሎት! መሬት ለመሬት እየተንከባለለ በመወድሱ ሲጠቀለልበትም ትዝ ይለኛል፡፡ ከቀትር በኋላ ጀምረን እስከምሽቱ ሦስት ሰዓት ቀጠልን፡፡ በሦስት ሰዓት ለጋዋ ጨረቃ ብቅ አለች፡፡ ለቅኔም አገዘችን፡፡ እንደምታውቀው የጨረቃ መባቻ ቀላል አይደለም፡፡ የጨረቃን መባቻ ጠብቆ በሽታ እንደሚቀሰቀሰው ሁሉ የቅኔ ስሜትም በአያሌው ይቀሰቀሳል፡፡ የጨረቃ ብርሃን ለባላገሮች የአጨዳ ወቅት ሲሆን ለቅኔ ዘራፊዎች ደግሞ ፍቱን መድኃኒት ናት፡፡ ጨረቃን ተጠቅመን ስንዘራረፍ አመሸን፡፡ በመጨረሻ የዋሸራው ሊቅ አንድ አስታራቂ ሐሳብ አመጡ፡፡" አለ ገሞራው እየሳቀ፡፡

"ምን አሉ?" አለ ታሪኩ

"ምንም አላሉም፡፡ ጨረቃዋ እስክትጠፋ ሲሰሙን ቆይተው ቁጭ ብለው ማደራቸውን ሲረዱ አፈፍ ብለው ተነሥተው ወደቤታቸው ገቡ፡፡ እኔ እየተከተልሁ መዝረፌን ቀጠልሁ፡፡ ተናደው ሰንጣራ ፍልጥ ቢወረውሩ መጥቶ ከግንባሬ ላይ ተተከለ፡፡" ብሎ ገሞራው ግንባሩን ለታሪኩ አሳየው፡፡ የለምፅ ምልክቱ አሁንም አለ፡፡ ይህን ሲያወሩ ቆይተው ወደ ዐራት ዐይናው ተመለሱ፡፡





"አንተ እንዳልኸው ያ ተማሪ እኛን በቅኔ ከፈተነን በኋላ "ቀለሙ ቢኖር ከቀለሙ ዘንድ እወስዳችሁ ነበር፡፡ ከዚያም እንደልባችሁ ትኩስ እንጀራ እየተመገባችሁ መወድስ ስትዘርፉ ትኖሩ ነበር የሚል ነገር ነገረን፡፡ ቀለሙን አንዳንዶች ተሰወረ ሲሉ ሌሎች ደግሞ ሞተ እያሉ ያሟርቱበታል፡፡ ቀለሙን ሳገኘው እንደምመጣ ቃል እገባለሁ ብሎ ተሰናብቶን ሄደ፡፡ እኔ ባሕር ዳር ድረስ በእግሬ ሸኘሁት፡ ፡ እሱ ሳይሆን አይቀርም ፈታኙ፡፡ በዐሥራ ዘጠኝ ዘጠና ስድስት ዓመተ ምሕረት በየቅኔ ቤቱ ዘወር ዘወር እያለ የዘራፊዎችን የቅኔ ዐቅም ይለካ ነበር፡፡ ለማንኛውም ይህንን ቅኔ እሱ ከነገረህ ምሥጢሩን ከየኔታ እንረዳለን፡፡ የተሰወሩት ቀለሙ እኒህ ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡ ቅኔዋ የእሳቸው ልትሆን ትችላለች፡፡" አለ ገሞራው፡፡

ገሞራው ተርኮ እንደጨረሰ ብድግ ብሎ በሶ ሊጠጣ ተዘጋጀ፡፡ ዛሬ ቀኑን ረሐብ ውሎበታል፡፡ ለወጉ ኮቸሮ ቢቀምስም ረሐቡ ሊወገድለት አልቻለም፡፡ አንዳንድ ቀን ይህንን የመሰለ ረሐብ ያጠቃዋል፡፡ ሰዓት ጠብቆ እንደ ሰው ምሳ ቀምሶ አያውቅም፡፡ መላ ጊዜውን ለትምህርት ሲሰጥ ምሳ መቅመስ አለመቅመሱን ይረሳዋል፡፡ ባዶ ሆዱን መሆኑን የሚያውቀው ሰውነቱ ተጎድቶ ሳብ በሳብ ሲሆንና አእምሮው ፍዝዝ ሲልበት ነው፡፡ አሁንም ረሐቡን ተከትሎ ሰውነቱ

የላብ ውቅያኖስ ሲቀዝፍ ተሰማው፡፡ በሶ ሊጠጣ ተነሣ፡፡ በሶ ሊመታ ሲጀምር ከፊሉ ዱቄቱ ተከነበለ፡፡ በጠባቧ ዋሻ በበሶ ዱቄት ተለቀለቀ፡፡ ታሪኩ ቀና ብሎ ሲመለከተው ገሞራው ቅጠል ቆርጦ ዋሻውን ይጠራርግ ጀመር፡፡ ጠርጎ እንደፈጸመ ወደበሶው ተመልሶ ወደጉሮሮው አንቆረቆረ፡፡ ታሪኩን ጋደም እንዳለ እንቅልፍ ቀደመው፡፡ ገሞራውም ጥቂት ሲያሰላስል ቆይቶ ተከለተለው፡፡

ኪነት በዮዳኒ(@gbw_dan)





# ፴፯

ስዉሩ ባለቅኔ

ከሳምንት በኋላ ዐራት ዐይናው ብቅ አሉ፡፡ ጨረቃ ሳትጠፋ ቀደም ብለው ነበር የመጡት፡፡ ታሪኩ በናፍቆት ተቀበላቸው፡፡ ዐራት ዐይናው ዝም ብለው ይናፍቃሉ፡፡ ድምፃቸው ይናፍቃል፡፡ ወጋቸው ይፍቃል፡፡ መዓዛቸው ሳይቀር ይናፍቃል፡፡ ቀጭን ሳቃቸው ትናፍቃለች፡፡ ቀለማቸው ይናፍቃል፡፡ ሌላው ቀርቶ አጭር ከዘራቸው ትናፍቃለች፡፡ ጭራቸው ይናፍቃል፡፡ ጭራ አያያዛቸው ይናፍቃል፡፡ ውበታቸው ይናፍቃል፡፡ የቀለም ለዛቸውማ መቃብር ወርደውም ቢሆን ይናፍቃል፡፡ የጉሮሯቸው ጥራት ይናፍቃል፡፡ በንግግራቸው ውስጥ ያለው ቅኔ ይናፍቃል፡፡ ውስጠ ወይራ አለበት፡፡ "የገበሬ ሽመቱ የሊቅ ተረቱ" ነውና ብሒሉ ተረታቸው ሳይቀር ይናፍቃል፡፡ በራሳቸው ላይ አልፎ አልፎ ጣል የሚያደርጓት ቆብ ቢጤም ትናፍቃለች፡፡ ደም ግባታቸው ይናፍቃል፡፡ ናፍቆታቸው ይናፍቃል፡፡ ሳምንት ቀርቶ ሦስት ሰዓት ሲለዩ ይናፍቃሉ፡፡ በዚች ሳምንት ብቅ አለማለታቸው በራሱ ይናፍቅ ነበር፡፡ ከሕይወታቸው ርጋታ ጎን ለጎን የአነጋግር ጭምትነታቸው ተመስጦ ያመጣል፡፡ ያስቆዝማል፡፡ ያመራምራል፡፡ የዐራት ዐይናው ሕይወት ብራና



Scanned with CamScanner

ነው። ያስተምራል። ገሞራው ከቀለሙ ጎን እስካለ ድረስ መጽሐፍ ባይዘረጋም ጭንቁ አይደለም። የገሞራው መጽሐፍ፣ ቀለሙ ሲሆኑ እንደ ፊደል ይቆጥራቸዋል። እንደብራና ያነባቸዋል። እንደ አቡሻህር ይቀምራቸዋል። እንደ ፀሐይ በብርሃናቸው ይመላለሳል። ተደምመው ያስደምሙታል። ቆዝመው ያስቆዝሙታል። ፈገግ ብለው ያስፈግጉታል። ቀለም ነግረው ያረኩታል። ወግ ነግረው ብዕር ያስመዝግልጡታል። በጽሑፍ በኩል የድርሰት ጥጉ፣ በወግ በኩል አድባሩ፣ በቀለም በኩል መምህሩ ናቸው። ከዚህ ጎን ለጎን አክብሮታቸው ይናፍቃል። ተግሳጻቸው ብርቅ ነው። ቀልዳቸውማ መቼም መች ለወግ አይመችም። ሰሞኑንም ናፍቀውት ነበር የሰነበቱት። እነሆ አሁን ከተፍ አሉ። ገሞራው የልቡን ሲጠይቃቸው ዐራት ዐይናው የልባቸውን ሲያወጉት ነው። በተዋነይ ዙሪያ የፈለገውን ያኽል ሲዘበዝባቸው በፍሥሓ እያደመጡ በምሉዕ ልብ ያወጉታል። ጠፍተው ሰንብተው ነበር። ይሄው መጡ። ዛሬ ግን ግብር ለውጠዋል። በሰሞኑ የዛፍ ፍሬ ይዘው ሲመጡ ነበር የሰነበቱት። ዛሬ ግን የጨበጡት ነገር የለም። ባዶ እጃቸውን ነው የመጡት። ከደረቅ ከዘራ በቀር ከእጃቸው ላይ ምንም ነገር የለም። ብቅ እንዳሉ

"እንደምን ሰነበታችሁ ልጆቼ! በጎም አይደላችሁ?" አሉ።





"እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነን።" አሉ ሁለቱም እጅ እየነሡ። ዐይን አፋሩ ገሞራው መሬት መሬት ያያል። ታሪኩ ዐይኖቹን በስርቅታ እየላከ ያስተውላቸዋል።

"በሰሞኑ ብቅ ሳልል ቀረሁ። ይቅርታ አድርጉልኝ።" አሉ ዐራት ዐይናው።

"ችግር የለውም። ያችን ጉደኛ ቅኔ እየመረመርን ነበር። ሥራ አልፈታንም።" አለ ታሪኩ።

"ደኅና ከሆኑ ችግር የለውም።" አለ ገሞራው ዝምታው የቅያሜ እንዳልሆነ ለማስረዳት።

"በደኅና ነው። በሰሞኑ እንዳያችሁት ብርዱ ኃያል ነበር። የዚህን ወር የጨረቃው ፍጻሜ ተከትሎ ዝርው ነፋስ በአያሌው ነፍሶ ነበር። ይህ ነፋስ ሲነፍስ ብዙ ድካም አያስፈልግም። ተሸብልሎ መተኛት ነው። የመጣውን እንቅልፍ በወጉ መጨለጥ!" አሉ ዐራት ዐይናው።

"እንዴት?" አለ ገሞራው የጨረቃ ፍጻሜ ያለው ንግግራቸው ትንሽ ጠጠር ብሎበት።

"በየወር በየወሩ በጨረቃ ሕፀፅ መጀመሪያ፣ በምላቷ ፍጻሜ ለአምስት ተከታታይ ቀናት ያኽል ዝርው ነፋስ ሲመጣ የሰው



Scanned with CamScanner

ልጆች አእምሮ ይዝላል፡፡ ሰውነት ይታክታል፡፡ በከተሜ ቋንቋ ድብርት ይሉታል፡፡ ባላገሮችም "ደበተኝ ውኃ አሙቁልኝ ቡን አፍሉልኝ" እያሉ ሰውነታቸውን ለማፍታታት ይሞክራሉ፡፡ ሰው ነንና የነፋሱ ጠባይ ሲቀየር አመላችን ጭምር አብሮ ይለወጣል፡፡ ዝርው ነፋስ በተቀሰቀሰበት ወቅት ተስፋ ቢስነት ወደውስጣችን ይገባል፡፡ በዚህ ሳምንት አእምሯችን እንደነፋሱ ዝርው ይሆናል፡፡ ቅዝት ይበዛብናል፡፡ አእምሮችን የሰጡትን ሰብስቦ ወደውስጥ ማስተጋባት አይችልም፡፡ በሰሞኑ መጥፎ ባስተምራችሁ ኑሮ አንዳች ቀለም ከአእምሯችሁ እንደማያድር ግልጽ ነበር፡፡" አሉ ዐራት ዐይናው ከአቡሻኽሩ ቀለም ጨልፈው አምጥተው፡፡

"ለእኔ አልገባኝም፡፡ ትንሽ ገለጥ ያደርጉልኝ?" አለ ታሪኩ

"አቡሻህሩ ይለፋችሁ፡፡ አድካሚ ቀለም ነው፡፡ ዝርው ነፋስ ሲቀሰቀስ የሚያመጣውን ጠባይ ግን በከፊል በምሳሌ ልግለጥላችሁ፡፡ ሰው በተለምዶ የሚኖረው ኑሮ ነው፡፡" ብለው አከሉበት፡፡

"እስኪላ ቤት ከነበራችሁ ታውቁታላችሁ፡፡ በእስኪላው የትምህርት ዓለም መምህሩ ዘወትር ወደ ክፍሉ ሲገባ ክለሳ ይሰጣል፡፡ ክለሳ የሚሰጠው ወድዶ አይደለም፡፡ ተማሪዎች ምን አልባት ዝርው ነፋስ በነፈሰበት ቀን የተማሩትን ቀለም





አእምሯቸው ካልተቀበለ መከለስ አለበት፡፡ በሀገራችን ያን ቀን ለይቶ የሚያውቅ ጠቢብ ስለሌለ ዘወትር መምህሩ ክለሳ ይሰጣል፡፡ ተማሪዎች ቢገባቸውም ባይገባቸውም የትናንቱን በመከለስ የማይጀምር አስተማሪ የለም፡፡ በእስኪላው ትምህርት ቤት የመምህሩ የሥራ መጀመሪያ ክለሳ ነው፡፡ በአብነቱም በኩል ያለፈውን ቀለም መከለስ የተለመደ አስተምሮ ነው፡፡ እኔ ግን በአእምራችሁ ላይ አንድ ቀን ግስገሳ፣ በነጋው ክለሳ እያልሁ አእምሯችሁን ማደንዘዝ አልፈልግም፡፡ አእምሯችሁ ስል በሚሆንበት ቀን አስተምራችኋለሁ፡፡ በጨረቃ ፍጻሜ ሌሊት መጥፎ ጥበብ መዝራት አልፈልግም፡፡ በሰሞኑ የቀረሁት ለዚህ ነው፡፡ የጨረቃ ፍጻሜ ይለፍ ብዬ ነው፡፡" ሲሉ ከቀመሩ ጥቂት ቀንጭበው ቀጠሉ፡፡

"አቡሻህሩን ተውት ይከብዳችኋል፡፡ ሌላ ጊዜ፣ ጊዜ ይኖረዋል፡፡ እንግዲህ መኻል ሀገር ሳለሁ በየጨረቃው ፍጻሜ ለብርዱም ስል ፈለገ-እሳትን እወስድ ነበር፡፡" አሉ እየሳቁ

"ፈለገ እሳት ደግሞ ምንድን ናት?" አለ ታሪኩ፡፡

"የሐበሻ አረቂ ናታ! ለብርድና ለእንቅልፍ ፍቱን መድኃኒት ናት፡፡ ከመኻል ሀገር ሳለሁ እቀማምስ ነበር፡፡ እኔና ኪነ ጥበብ አብረን ጨልጠናታል፡፡ እኔ እሷን ስቀምስ ሳቅ ሳቅ

ይለኝ ነበር። ኪነ ጥበብ እሷን ፉት ካለ መለኪያውን እንደጨበጠ እንቅልፍ ይጥለዋል። አረቂዋ አንድ ስትሆን ተፈጥሯችን ልዩ ልዩ ነው። እኔን በሳቅ፣ ኪነ ጥበብን በእንቅልፍ ታሰናብተናለች። አሁን ግን በአፌ አድርጌአት አላውቅም።" ብለው ዐራት ዐይናው ቀጭን ሳቃቸውን ስቀው ሲጨርሱ

"መወድሱን መረመራችሁት?" አሉ ዐራት ዐይናው።
"እንደአቅማችን መረመርነው ብለናል" አለ ገሞራው

መወድሱ "ዴንሳ እመኒ ወተወከሊ ይልማና።

እብን በከመ ልማዱ እስመ ኮነ መና።"

ሲሆን መወድሱን ቀለሙ የሚባል ሰው እንደዘረፈው በጭምጭምታ ሰምተን ነበር። ምን አልባት ይህ ቅኔ የእርስዎ ቅኔ ይሆን?" ታሪኩ ፈጥኖ ጠየቃቸው።

"እኸ! እኸ! የምን አልፎ ማቃጨል ነው! ቅኔውን እንደሸንብራ ቆርጥመነዋል ብላችኋል፤ መጀመሪያ ቅኔው ምን ማለት ነው?" አሉ ምንም የማያውቁት ለማስመሰል

"ዴንሳ ተረጅልኝ እመኝ ይልማና።





ድቡልቡሉ ድንጋይ መና ሁኗልና።" ማለት ነው።" አለ ታሪኩ።

"ምሥጢሩንስ እንዴት አያችሁት?"

"ውስጠ ምሥጢሩን አናውቅም። ባለቅኔውም በሕይወት እንዳሉ አይነገርም። ተሰውረዋል። ወይም ሙተዋል የሚል ወሬ ነው በየቅኔ ቤቱ የሚወራው።" ብሎ ታሪኩ ሞታቸውን አረዳቸው።

ዐራት ዐይናው ሞታቸውን ሲሰሙ ፈገግ አሉ። ተሰውረዋል የሚለው ግን አልገረማቸውም። ገቢራዊ አድርገውታልና! ከወሉ ሊቆች የሚለዩበት ቀዳሚው ምሥጢርም ይኸው ስዋሬው ነው። ወሉን እንደአጥቢያ ኮከቦች ያደመቋት ሊቆች ሲያልቁ ቀለሙ ብቻቸውን ቀርተዋል። በኀብስተ መናው በኩል መልአከ-ሞትን በመገዘታቸው ፍሥሓቸው ምሉዕ ሆኗል። በዚህ ግን ከወሉም ሆነ ከዓለም ጠቢባን ልዩ ናቸው፡ ፡ ከስዉሩ ዓለም ካሉ ጠቢባን በቀር የሚተካከላቸው ጠቢብ የለም። በስዉሩ ዓለም ባሉ ሴቶች በኩል የሞት መግቻ በመዳፋቸው ነው።

ጥቂት ሲተክዙ ቆይተው "መወድሱ የእኔ መወድስ ነው።" ሲሉ ጉድ ጎለጎሉ።

“ቅኔው የመናውን ምሥጢር ይገልጣል? የሞት መግቻ የሆነው መና ከድንጋይ የሚሠራ መና ነው?” አለ ታሪኩ ቸኩሎ።

“እረ በጭራሽ! ድንጋይ መቼ ዳቦ ቆሎ ሆኖ ያውቅና!” ብለው ዐራት ዐይናው አረጋጉት።

“ታዲያ መወድሱ ድቡልቡሉ ድንጋይ መና ሁኗልና።” ሲል ምን ማለቱ ነው?” ይበልጥ ድምፁን ከፍ አድርጎ ዐይኑን ጉልጉሎ ጠየቃቸው።

“እረ ጉድ ነው ወንድሜ?” ብለው መወድሱን ማብራራት ጀመሩ።

“ይቺን ቅኔ የዘረፍኂት እኔ ነኝ። በበቀደም እንዳነሣሁት እኔና መሼ በከንቱ ለልቅሶ ዋሸራ ሄድን። ከዋሸራ መልስ ወንዙ ሞልቶ ጠበቀን። ባላገሩ በእንግዳ ወግ ሳይቀበለን ቀረ። ዋርካው ሥር አደርን። በዚህ ጊዜ መሼ በከንቱ ጥበብ ተጠቅመው የመና ቁራሽ አወረዱ። በልተን እንደ ጨረስን

“ዴንሳ እመኒ ወተወከሊ ይልማና።

እብን በከመ ልማዱ እስመ ኮነ መና” ብዬ መወድስ ዘረፍሁ።

ትርጉሙም





“ዴንሳ ተረጅልኝ እመኒ ይልማና።

“ድቡልቡሉ ድንጋይ መና ሁኗልና።”

ስል በግእዝ ቋንቋ ዘረፍሁት። ቅኔዋ የመጣችው ዝም ብላ አይደለም። ያን ጊዜ መሼ በከንቱ በነፋስ ያመጡ መና ድቡልቡል ድንጋይ ቅርጽ ነበረው። በዚያ ላይ ድንጋዩን መና አድርገው የመገቡኝ መስሎኝ መወድሱን አበረከትሁላቸው። ይህን የዘረፍሁት በታሪክ እንዲቀመጥ ፈልጌ ጭምር ነበር ይኸውና ከእናንተ ጆሮ ሳይቀር ደርሶ አገኘሁት። ድሮ ከተከሰተ በቀር የሚያውቀው አልነበረም። አሁን እሱ ሙቷል።” ሲሉ የታሪክ ዳራ አስጨበጧቸው። ከዚያም አከሉበት፡

“ከዕለታት ባንድ ቀን ከዋርካው ሥር ቁጭ ብለን ስናወጋ የመሼ በከንቱ ነገርን ለመምህሬ ነገርኂቸው። እሳቸውም ሰምተውት መሰለኝ ያ ከንቱ ነገር ነው። በዚያ ላይ ለመሆኑ ሰው የደከመበት ነገር ምን ይሠራልኻል? ሲሉ ጠየቁኝ። በዚህ ዓለም ለእንጀራ መውጣት መውረድ ሰልችቶናል። ቁጭ ብዬ ማንበብና መፈላሰፍ እፈልጋለሁ። በዚያ ላይ ሊቅ ለእንጀራ ሲኖር ደስ አይልም። ሊቅነት ይረከሳል። እውቀት በቁራሽ እንጀራ ይሸጣል። የዓለም ሀገራት ለምሁሮቻቸው የተለየ አክብሮት አላቸው። የእኛ ሀገር ሊቆች ግን

ለክርሣቸው ሲሉ እውቀት ይሸጣሉ:: ይህ የሊቆችን ክብር ዝቅ የደናቁርትን ስንፍና ከፍ ያደርጋል:: በዚህ መንገድ መሄድ ለእኔ ስሜት አይሰጠኝም:: የእንጀራዬ ጉዳይ በኅብስተ መናው እንደ ተዋነይ ከተሸፈነ ወደፊት ተረጋግቼ አዳዲስ ፈጠራዎችን መፍጠር እፈልጋለሁ:: በዚያ ላይ ድርሰት ነፍሴ ናት:: ደራሲ መሆን እሻለሁ:: ደራሲ ደግሞ እንባቢ እንጂ ሆዳም መሆን የለበትም:: የሆዱ ነገር በተዋነይ መና መሸፈን አለበት ብዬ አምናለሁ አልኳቸው:: በአስተሳሰቤ ተደመሙ:: ሊያርፉ ሳምንት ሲቀራቸው የመናውን ምሥጢር ነገረው ወደ ስዉሩ ዓለም ላኩኝ:: ስመጣ መናው በድንጋይ አምሳል ጠበቀኝ:: አሁን ሳስበው መሼ በከንቱ የስዉሩን ዓለም መና በደመና የሚወስዱት ይመስለኛል:: ያም ባይሆን ደቀኛው በደመና እየተጫኑ እንደሚወስዱላቸው እገምታለሁ:: በኋላ ሊሞቱ የቻሉት መናው ቀርቶባቸው መሰለኝ:: አሁን ግን በመኻል ሀገር ድንጋዩን መና የሚደርግ ሊቅ ነበር:: ሞተ እየተባልሁ ነው አሉ:: በሩ ሥላሴ ላይም መርዶ ተጠርቶብኛል አሉ:: እኔ ግን መናውን ቀምሼ በሕይወት እየኖርሁ ነው::" ብለው

"በሉ ከነገ በኋላ የሞት መግቻውን መና ማምጣት ወደ መጨረሻው ዐርባ ዐራቱ ወደሚባለው ስለምትሄዱ ዛሬ





ከጠቢቡ ሖረ ጋር ተጫዋወቱ:: ይፈልጓችኋል::" ብለው ወደ ጠቢቡ ሖረ አደረሷቸው:: ማረፊያቸው ቅርብና ቅርብ ነው::

ቤት በዮዳ(@gbw_dan)
Telegram Channel

## ፴፱

ወዲ አፈ ወርቂ

ከጠቢቡ ሖረ ቤት ሲደርሱ ጀንበር ጠልቃ ጨረቃ ወጥታ ነበር። የጨረቃ አጃቢዎችም ብቅ ብቅ ብለዋል፡፡ በተለምዶ ሰብአ ሰገል የሚባሉ ከርታታ ኮከቦች ናቸው፡፡ ዘላለም በምዕራብ በኩል ይወጣሉ፡፡ የሰማይ ጌጥ የምድር ፈርጥ ናቸው፡፡

"እንዴት ነው? ዐለቱ ተመቻቻችሁ?" አሉ ጠቢቡ ሖረ፡፡

"አዎን ተመችቶናል፡፡ እንዲያውም ስለ አንድ ሊቅ ጉዳይ አንሥተን ከኅብስተ መናው ወግ ጫፍ ጫፉን እያወራን ነበር፡፡ ዐራት ዐይናውን ሳንጠይቃቸው ወደ እርስዎ መጣን፡፡" አለ ገሞራው፡፡

"ማን ናቸው እሳቸው?" አሉ ጠቢቡ፡፡

"በስም የሚታወቁ ሊቅ አይደሉም፡፡ በደርግ ዘመን በስዋሬ ተጠቅመው ኅብስተ መናውን ገቢራዊ ያደረጉ የሊቅ ታሪክ ትዝ ብሉኝ እያወራሁ ነበር፡፡" አለ ገሞራው





"እስኪ ለእኔም ትረፉኝ?" አሉ ርሳቸው የማያውቁት ታሪክ መስሏቸው፡፡

"በስሚ ስሚ የሰማሁት ታሪክ ነው፡፡ አጥጋቢ ነገር የለውም፡፡ የሆነው ሆኖ አንድ ሊቅ በዘመነ ደርግ ወደ ሱዳን ጠረፍ ወርደው ነጭ አብሾ ሲፈልጉ በሽፍቶች እጅ ወደቁ፡፡ ወዲያው ግን ተሰወሩ፡፡ እንደ ተሰወሩ ኅብስተ-መና የሚባለውን ጥበብ ተጠቀሙ ሲባል ሰምቼ ይህንን ወግ ለታሪኩ ሳወጋው እርስዎ ደረሱ፡፡" አለ ገሞራው፡፡

"በመቼ ዓመተ ምሕረት የነበሩ ሊቅ ናቸው?" አሉ ጠቢቡ ሖረ፡፡

"ንጉሡ ከተገረሰሱ በኋላ በአሥራ ዘጠኝ ሰባዎች ውስጥ ይመስለኛል፡፡ የታሪክ ግጥምጥሞሹም ከዚህ ጋር ይመሳሰላል፡፡" አለ ገሞራው፡፡

"እንዴት? እንዴት?" አሉ ጆራቸውን ወደ ገሞራው አቅጣጫ ዘንበል አድርገው፡፡

"በዚህ ወቅት የሀገራችን ወጣቶች የአብዮቱ እሳት ራት ሆነው ነበር፡፡ ዘመናዊቷን ኢትዮጵያ እንፈጥራለን ያሉ ወጣቶች ከከተማ ፈነዱ፡፡ ከተማው በአብዮት እሳት ሲቀጣጠል የዘውዱ መንግሥት እንደ ነዳላ ጉሽጉሻ

መፍረክረክ ጀመረ። ተፍረክርኮ ብቻ አልቀረም። ምስጥ እንደበላው ቁልቋል ተገረደሰ። ወታደራዊ መንግሥት ሀገሪቷን በመዳፉ አድርጎ መሬት ላራሹን ሲያውጅ ሕዝቡ በደስታ አበደ። ያ ፍሥሐ ግን ሊቀጥል አልቻለም። መሬት ላራሹ ከታወጀ በኋላ ወታደራዊው መንግሥት በሀገር ፍቅር አስመስሎ በተራማጅ ወጣቶች ላይ እሳተ-መለኮት የሆነ አብዮት አቀጣጠለ። መንታ የተወለዱ ወጣቶች እንደ አመጣጣቸው መንታ መንታ እየሆኑ ከዚህ ዓለም ተሰናበቱ። በአንድ ዕለት ተዘርተው በአንዲት ዕለት በቅለው እንደ ፈረደባቸው በአንዲት የቀይ ሽብር ምሽት በፍየል ወጠጤ መዝሙር ተሸኙ። ቀሪዎች ዱር ቤቴ ብለው ከከተማ ወደ ጫካ አፈገፈጉ። በዚህ ወቅት የዋሸራ የቅኔ ተማሪዎችም የጥበብ አብዮት ማቀጣጠል ጀምረው ነበር። ያም ማለት በጃንሆይ ዘመን በዐሥራ ዘጠኝ ዐርባ ዘጠኝ ዓመተ ምሕረት ከዛሬ ሥልሳ ስድስት ዓመት በፊት ዐሥራ አምስተኛው ዐቢይ ቀመር ተጀምሮ ነበር። ይህንን ተከትሎ የጥበብ አብዮት ጭምር መፈንዳቱ እሙን ነበር። በዚህ ወቅት የጎንጅ ሊቆች ታብርን በመክሰት ሲተጉ በሌላ ቦታ የነበሩ የቅኔ ተማሪዎች ደግሞ ጠረፍ ወርደው ነጭ አብሾን እያመጡ ለቅኔ አብነት እያደረጉ ነበር። በዚህ ጊዜ ነበር አንድ ሰው ያችን ነገር ፍለጋ ወደሱዳን የወረዱት። አካሄዳቸው የወባ





መድኃኒት ከሚረጩ ሐኪሞች ጋር ተመሳስለው ነበር ይባላል። ሐኪሞቹ መንደር ለመንደር እየተዟዟሩ የወባ መድኃኒት ሲረጩ የቅኔው ሊቅ ዱር ለዱር ሄደው ከነጭ አብሾ ጋር ተገጣጠሙ። ነጯን ይዘው ወደ ዋሸራ ሲመለሱ ግን በእኒህ ከከተማ ወደጫካ በኮበለሉ ቡድኖች እጅ ወደቁ። በዚህ ጊዜ የመጀመሪያውን ስዋሬ፣ ሁለተኛውን ኅብስተ-መና ተጠቅመው በሕይወት እንደተረፉ በየቅኔ ቤቱ ይወራል።" አለ ገሞራው የራሳቸውን ታሪክ ሳያውቅ ለራሳቸው እየተረከ።

ጠቢቡ ሖረ ፈገግ ብለው "ያ ሰው አሁን ድረስ በሕይወት ይኖር ይሆን?" አሉ።

"ምኑን አውቄ ብለው ነው!" ብሎ ገሞራው ተከዘ። ጥቂት ሲያቅማሙ ቆይተው

"ብዙ አትድከሙ። ያ ሰው እኔ ነኝ። በተጠቀሰው ዓመተ ምሕረት የዋሸራ የቅኔ ዘራፊ ነበርሁ። የሆነ ነገር ፈልጌ ወደ ሽንፋ በረኃ ወረድሁ። አካሄዴ አንተ እንዳልኸው የተለመደውን ኀሠሣ አልነበረም። እሷን ያገኘኋት አልፌ ስሄድ ነው።" አሉ እንደ ዋዛ። ከዚያም ቀጠሉ።

"በወቅቱ በታብር በኩል ተስፋ የቆረጡ የቅኔ ዘራፊዎች ጭምር አብረውኝ ነበሩ። እነሱ ነጭ አብሾ ፍለጋ ሱዳን



Scanned with CamScanner

ድንበር ድረስ አብረውኝ ወረዱ። በዚያ ወቅት አብዛኛው የቅኔ ተማሪዎች በመጸው ወራት ወርደው በጸደይ ይመለሱ እንደ ነበር ግልጥ ነበር። አብዛኛው ተማሪ ግን በፀደይ መመለሱን በራሱ እጠራጠራለሁ። በዚያው እንደ ወጡ የቀሩ እልፍ ናቸው። ከእኒህ እልፍ ጆቢራዎች መኻል በረሃ ወድቀው ወድቀው የቀሩ እንዳሉ ሁሉ በእግረ መንገዳቸው የጠቢባንን ዓለም የተቀላቀሉም አያሌዎች ናቸው። ስለ እኒህ ወደ ፊት እናወጋለን።" ብለው ከርታታ ኮከቦች ትዝ አሏቸው። እልፍ የቆሉ ተማሪዎች በግድ ወደ እሳት ተማግደው የአሞራ ሲሳይ ሆነ ቀርተዋል። የሰሜኑ ጦርነት ሊቆችን በልቷል።

"አሁን እንዳላችሁት በዐሥራ ዘጠኝ ሰባዎች ውስጥ የሀገራችን አብዮት እሳት ሆና ሀገር እየለበለበች ነበር። የሀገሬ ልጆች ርስ በርስ እየተፋለሙ ነበር። ቡድን ፈጥረው ውረድ እንውረድ ተባብለው ከከተማ ወደ ጫካ ገብተው የጦርነት ነጋሪት ጎስመው ነበር። ከቡድኑ መካከል ቀዳሚዎች ዱር ቤቴ ብለው ጠረፍ ጠረፉን በተቆናጠጡበት ወቅት የዋሸራ የቅኔ ዘራፊ ሁኜ ወደታች ወረድሁ። ባጋጣሚ ዋናዋ ሳትሆን ሁለተኛዋ ከእጄ ገባች። በሸንበቆ ዐፅቅ ሰግስጌ በአኮፋዳዬ መትቼ ወደ ዋሸራ ስመለስ በእኒህ ቡድኖች እጅ ወደቅሁ። ይዘው መረመሩኝ። ምርመራቸው ለወግ አይመችም። ግርፋት ጭምር ነበረበት። ገልብጠው





ገርፈውኛል። ዱላው ሲጸናብኝ ወደበረሃ የመጣሁበትን ምሥጢር ዘከዘክሁላቸው። የአብሾዋን ፍሬ ከአኮፋዳዬ አውጥቼ አሳየኋቸው። ለጊዜው የደርግ ሰላይ መስያቸው ደሜን ፉት ሊሉት ነበር። አጥብቀው ሲመረምሩኝ እልም ያልሁ ቀርፋፋ የቅኔ ዘራፊና ወንጌላዊ እንደሆንሁ ተረዱ። ያም ሆኖ ሊለቁኝ አልቻሉም። ሻሽ ገዝተው ጠመጠሙልኝ። በፊት "ከመጠምጠም መማር ይቀድም" ነበር ወጉ። ያን ጊዜ ከመማር መጠምጠም ቀደመ። ሱማያ ዘንግ ገዝተው በእጄ አስጨበጡኝ። ከበረኻ ዕፅ ቆርጠው መስቀል ሠርተው ሊቀ ካህናት አድርገው ሾሙኝ። የመጀመሪያ የቡድኑ ሊቀ ጳጳስ እኔ ሳልሆን እቀራለሁ? እረ ነኝ። ከእኔ በኋላ ለእግዜር በጎች እውነተኛ እረኞች የተሾሙ አይመስለኝም። ለፍየሎች ካልሆነ በቀር።" ብለው ፈገግ ካሉ በኋላ

"መስቀል አስጨብጠው ካህን ካስመሰሉኝ በኋላ ጉዳቸውን አመጡ።" አሉ ጠቢቡ ሖረ ፈገግ ብለው።

"የምን ጉድ እንደጣሊያን ጳጳሳት መድፍ ይባርኩ ተባሉ?" አለ ታሪኩ እየሳቀ።

"እሱስ ቢሆን የአባት ነበር። እነሱ ግን በእንተ ማርያም ስል ቁራሽ እየዘከረ ላስተማረኝ ሕዝብ የሐሰት ነቢይ አድርገው

ሊሾሙኝ ከጀሉ። ለዚህ ነው ወደስዋሬው ጥበብ የገባሁት።" ብለው ከሥር ሳቡት።

"በመዳፋቸው ሥር ስወድቅ ጊዜ ይህንን የበረኃውን ሕዝብ ሰብስበህ "የአንድ ላም ወተት የአንድ በሬ እሸት ለዓለም ይበቃል" የሚለው ትንቢት የሚፈጸው እኒህ ቡድኖች ቤተ መንግሥት ሲገቡ በትረ መንግሥት ሲጨብጡ ብቻ ነው። ከጎናቸው ቁማችሁ ተዋጉ። ደርግ ይደምሰስ። እኒህ ቡድኖች ዐርባ ዓመት በፍቅር ይገዛሉ። ቀጥሎ ቴዎድሮስ የሚባለው የመጨረሻው ንጉሥ ይነግሣል። ከእሱ በኋላ መልካም ንጉሥ እንጂ ክፉ ንጉሥ ተመልሶ አይመጣም። ከቴዎድሮስ በኋላ ተከታታይ የሚመጡ ነገሥታት የኢትዮጵያ ፀሐዮች ናቸው። ከዚያ በኋላ ጌታ ይመጣል። እኒህ መንግሥት ሲይዙ ያንድ ላም ወተት ለዓለም ይበቃል እያልህ ሕዝቡን ሰበክልን። ቆለኛውን አሳምንልን።ቆለኛው ካመነ ደርግን እንደመስሰዋለን ብለው አስገደዱኝ። ውዳሴ ማርያም በደገምሁበት አንደበቴ የውሸት ስብከት ሰብኬ ሕዝብን መዋሸት አልፈልግም ብዬ እምቢ አልኗቸው። አስረው ደበደቡኝ። ለማናቸውም ብዬ ዘመኑን በቀመር ቀመርሁት። ወፍ የለም። እርግጥ ነው በአፈ ታሪክ ቴዎድሮስን የመሰለ ንጉሥ ሲመጣ የአንድ ላም ወተት የአንድ በሬ እሸት ለዓለም ይበቃል ይባል ነበር። ቴዎድሮስን የሚመስል ንጉሥ ከመጣ በኋላ ዐርባ ዘመን





ይነግሣል። ከዚያ በኋላ የጌታ ምጽአት ይደረጋል። ጌታ መጥቶ የጌታ ቀን ይገለጣል እያሉ ሕዝቡን የሚያወናብዱ ስም ወረስ ባሕታውያን ነበሩ። የኢድዩ ነቢያት ደግሞ ዋጃንሆይ የዘውድ መንግሥት ከጀርመን ድጋሜ ይነሣል። ልብሱ ሽማ አክሊሉ አክሊለ ወርቅ ነው። ይህ መንግሥት በጃንሆይ ዙፋን ሊተካ ነው። በዘውዱ መንግሥት እመኑ። ለእኛ ድጋፍ ስጡ" እያሉ ቆለኛውን የሚያምታቱ የውሸት ካህናት ነበሩ። እኔም የቡድኑ ሊቀ ጳጳስ ሆኜ የተሸምሁት በዚህ ውጥንቅጥ ዘመን ነበር። እንደነገርኋችሁ የአንድ ላም ወተትን ሰበክ ሲሉኝ ግራ ገባኝ። ግራ ሲገባኝ ስዋሬውን ተጠቀምሁ። የአንድ ላም ወተት የአንድ በሬ እሸትን ሰብኬ ሕዝብ ከማደናግር ብሰወር ይሻለኛል ብዬ ከፊታቸው ተሰወርሁ። ምንም ሊያደርጉኝ አልቻሉም።" አሉ ሖረ።

"እንደ እሱ! በታሪክ እያሾሞነሞኑ ያምጡትማ!" ሲል ታሪኩ በውስጡ ተናገረ።

ሖረ ግን ደቅማውን ተደግፈው ቀጠሉ።

"ያንድ ላም ወተት የአንድ በሬ እሸት ስብከት እውን እንደማይሆን ለማወቅ ጊዜ አልፈጀብኝም። መጻዒውን ዘመን በቀመር ስቀምረው ወደፊት የሚመጣውን ዘመን ቁልጭ አድርጎ ገለጠልኝ። ቡድኑ ግን ቆለኞችን በስብከት ወደ ዐውደ



Scanned with CamScanner

ውጊያ ሰቦ በአርሶደሮች ሰብከት ቤተ መንግሥት ሲገባ ይዳደው ነበር። እኔ ምኔ ሞኝ ነው። በባዶ ተነሥቼ የአንድ ላም ወተትን እሰብክ ዘንድ ሕሲናዬ መቼ ይታዘዘኛል። መስቀል እንዳስጨበጡኝ ሻሽ በራሴ እንደደገለልሁ ከፊታቸው እልም ድርግም አልሁ። ይቺን ይወዳል የተዋነይ ልጅ ስል ምራቁን ጺቅ አልሁባቸው። ርስ በርሳቸው ተተረማመሱ። ከፊሉች ወደ እኔ አቅጣጫ ተኮሱ። ወዲያው ዋይታና ጫጫታ ተጀመረ። የሻቢያን የውስጥ ምሥጢር አወቅን ተራቀቅን ያሉት ወገን 'ኢሳይያስ አፈ ወርቂ ቀለደብን። ወዲ አፎም ጉድ ሠራን። ወዲ አፎም ቀለደብን። ወዲ አፎም በዕፀ መሰውር በመኻላችን ገብቶ ወጣ። የቄስ አፈወርቂ ልጅ ሰልሉን ተሰወረ' እያሉ የእኔን ስዋሬ ለኢሳይያስ ሰጡት። እኔ ተሰውሬ እስቅ ጀመር።" አሉ አሁንም እየሳቁ።

"ኢሳይያስና ርስዎን በምን መልኩ አመሳሰሏችሁ?" አሰ ታሪኩ ግር ብሉት።

"ምን ያመሳስለናል ብለህ ነው። በዚያ ወቅት የአሁኑ የኤርትራው መሪ ኢሳይያስ አፈ ወርቂ ዕፀ-መሰውር አለው እየተባለ ይጠረጠር ነበር። በወቅቱ ሰውዬው እንደብረት የጠነከረ የጦር ሊቅ ነበር። እንዲያውም በጦር ሜዳ የተለየ ብቃት አለው ይላሉ። በተፋፋመው ዐውደ ውጊያ መኻል





ገብቶ ሲያዋጋ እሱ ለዐይን አይታይም ይባላል። በወቅቱ ጠላት ሲከብበው ይሠወራል እየተባለ ስለ ኢሳይያስ አፈወርቂ በሰፊው ተወርቷል። ለዚህ ነው ወዲ አፈወርቂ መኻላችን ገብቶ ወጣ ሲሉ የኢሳይያስን ቅጽል የሰጡኝ።" አሉ ጠቢቡ ሶረ። ገሞራውና ታሪኩ ዐለቱ እስኪናጋ ተሳሳቁ።

"ኢሳያይስኮ አሁንም በሕይወት አለ። ለመሆኑ ይሰወር ይሆን? ወይስ የደርግን ሠራዊት ሥነ ልቦና ለመስለብ የተጠቀመው የጦር መላ ነው?" አለ ገሞራው።

"እሱን ኢሳይያስ ያውቃል። በእርግጥ ቅኔ ቤት ሳለሁ ከኤርትራ የመጣ የቅኔ ዘራፊ ነበረ። ነገሩን አንሥቼለት ኢሳይያስ እንደ ሌሎች መሪዎች አጃቢና ከብካቢ አያበዛም። ልቅሶ ለብቻው ይሄዳል። የድሮ የጦር ጓዶችን ሳይቀር በእግሩ ከቤታቸው ድረስ እየሄደ ይጠይቃል። በዚህ ጊዜ አጃቢ የለውም ይባላል። ጠላት ሊያጠቃኝ ይችላል ብሎ ከገመተ ግን በእግሩ እየተራመደ ድንገት ከመኻል መንገድ ይሰወራል እያሉ የኤርትራ ሕዝብ እንደሚያምኑ አውግቶኛል። ይህ ብቻ አይደለም! በወቅቱ የቅኔው ተማሪ ወጉን መነሻ አድርጎ ቅኔም ዘርፎበት ነበር። ቅኔው በተዘረፈበት ምሽት እኔና ያ ኤርትራዊ የቅኔ ዘራፊ በሳቅ ሙቲት ብለን ነበር። በግሌ ግን ሐሜታውን ማረጋገጥ አልቻልሁም። በእርግጥ ኢሳይያስም

ሆነ ሌሎች ተዋጊዎች የተፋላሚአቸውን ሥነ ልቦና ለመስለብ ሕዝቡን ቶሎ ለማሳመን ተመሳሳይ የጦር መላ አላቸው:: የራያ ሰዎች ደግሞ ስመ ጥሩው የጦር ሰው ኀየሉም እርሷያ ይሰወራል እያሉ ያወሩ ነበር:: ይህ ሊደንቅህ አይገባም:: የኮርያ ዘማቾች የበሬ ሥጋ ሲበሉ ከሞተ ወታደር አስከሬን ላይ ቆጭ ብለው ነበር:: የነጭ ሥጋ የበሉ ለማስመሰል ከተፋላሚአቸው ሬሳ ላይ ቁጭ ብለው የበሬ ጮማ ሲቆርጡ የሰሜን ኮርያ ወታደሮች ብትንትናቸው ወጥቷል:: የጦር ሰው በጠላቱ ላይ የሥነ ልቦና ጫና ያደርሳል ብሉ የገመተውን በሙሉ ይጠቀማል:: የኢሳይያስ አፈወርቂ ታሪክም ከጦር ሜዳ የዘለለ ታሪክ ሲሆን የሚችል አይመስለኝም:: የመሰውሩ ወሬ ግን የሥነ ልቦና መስለቢያ ይመስለኛል::" ብለው ከተረኩ በኋላ ወደራሳቸው ሕይወት ተመለሱ::

"ለእኔ ሰዋሬው በትክክል ሲሳካ ስንቅ አልነበረኝም:: ወደፊት እንዳልሄድ ጊዜው መሽቶ ነበር:: በዚያ ላይ ጦም ሰንብቼ በረሐብ ተዳክሜ ነበር:: በዚህ ጊዜ ከሰዋሬ ወደመገለጥ ወጥቼ በእንተ ማርያም ማለት ጀመርሁ:: ያን ጊዜ ይህ የኀብስተ መናው ምሥጢር ኑሮኝ ቢሆን እጠቀምበት ነበር:: በሰዋሬው ግን ይኸውና ያን ክፉ ዘመን አልፌ ታሪኬን ለመንገር በቃሁ: : ታች አምና ያን የሰዋሬ መጽሐፍ መኻል ሀገር ትቸው





መጣሁ:: የበለጠ ሳገኝ ጊዜ መጽሐፉን ወርውሬ ወደዚህ ስዉር ዓለም ተቀላቀልሁ:: 'ያን ጊዜ ኀብስተ መናው ግን እናንተ እንዳላችሁት በእጄ አልነበረም::" ብለው በዐሥራ ዘጠኝ ሰባዎች አካባቢ ከሞት አፍ ያመለጡበትን ታሪክ ቆንጥረው በሁለቱ ደቀ መዛሙርት ልቦና ዘርተው ዝም ሲሉ

"እኛ ኢትዮጵያውያን ስንባል ብዙ ይቀረናል:: ይህን የመሰለ ጥበብ አስማት ብለን ገድፈነዋል:: በእውነት እኛ ኢትዮጵውያን ገና ሞኞች ነን:: ተላሎች ነን:: ይህንን የመሰለ ተአምራዊ ታሪክ የሠሩ ሊቆች እንደ ዋዛ ሲያልፉ እያለቀሰን ቀብረናቸዋል:: በዚህም ሀገር በድለናል:: ትውልድ አምክነናል:: ለዚህ ቅጣት ያስፈለገናል:: ግን ደግሞ ፈጣሪ ሳይደግስ አይጣላም:: ለዘር እናንተ አላችሁ:: ይበሉ በደንብ ያስተምሩን:: ታሪኩንም ሳይሰስቱ ይለግሱን:: ታሪኩ እንደ ወረደ ይከትበዋል:: እንደ ዋዛ የሰማውን በወግ በወጉ አድርጎ ወደድርሰት ያመጣዋል:: በስዉሩ ዓለም የሰማውን ምሥጢር በከፊል ለቀሪው ትውልድ እንዲጽፈው እየነገርሁት ነው:: እሱም ተስማምቷል:: የመጽሐፉን ስምም ክርታታ ኮከቦች በለው ብዬ ርእስ መርጬለታለሁ:: ጽፎ ሲፈጽም ወደመኻል ሀገር ይላካል:: ይህ ትውልድ ተስፋ እንዳለው ያውቃል::" አለ ገሞራው:: መልካም ብለው ጥቂት ሲያወጉ ቆይተው ወደ ዶቅማው ተመለሱ::



Scanned with CamScanner

# ፴

## ክርታታ ኮከቦች

ገሞራውና ታሪኩ ክርታታ ኮከቦች ሆነዋል። አሁን የቀረው መልአከ-ሞትን መገዘት ብቻ ነበር። ይህ ሳምንት ወደ ሴቶች የስዋሬ ዓለም ገብተው ኅብስተ-መናውን ቀምሰው ሞትን የሚገዝቱበት ወር ነው። እሱን እየጠበቁ ክርታታ ኮከቦችን እየጠየቁ ዓሥራ አንድ ወራትን አሳለፉ። ደቅማውን ተደግፈው ቁጭ ብለው ካደሩ በኋላ የመጨረሻው ደወል ተደወለ። ዐራት ዐይናው የሆነ ነገር በእጃቸው ጨብጠዋል። ወይራው ከወይራ ከዘራ በቀር ያንጠለጠሉት የለም። ደቀኛውና ጠቢቡ ሖረ በምሥራቅ በኩል ከተፍ አሉ። ጉዞው ተጀመረ። ወደ መናው ዓለም። ሞት ራሱ ሊሞት ቅጽበት ቀርቶታል። እነሆ አሁን በጳደይ የወር ቀመር ዘጠና አንድ ቀን ሊፈጸም ተቃርቧል። የጳደይ መባቻ ተበሰረ። ጨረቃም በምሥራቅና በምዕራብ መስኮቶች ስትንከራተት ባጅታ ወደጥንተ-ተፈጥሮዋ ተመለሰች። በተፈጠረችበት መስኮት ወጥታ በተፈጠረችበት መስኮት ትገባ ጀመር። ወዲህም የጳደይን ወር ተከትሎ የጌታ ቀን ደረሰች። ወሩ የጳደይ ወር ሲሆን የጌታን ቀን የስዉሩ ዓለም ሴቶች ብቻ ጠንቅቀው የሚያውቋት አንዲት ቀን ናት። ለወንዶች ግን አሁንም





ስዉር ናት። በዚች ቀን ገሞራው በልጅነቱ ዘኢያገድፍ ቀምሷል። ከልጅነቱ ጀምሮ ቀለም ጠብ የማይለው ለዚህ ነበር። የፀደይን ወር ጠብቆ መወድስ የሚፈላበትም ከዚህ የተነሣ ነው። የእሳት ሠረገላው እየገነፈለ አእምሮው በእውቀት እየንጎለ ዝረፍ ዝረፍ ሲለው መወድስ ሲዘርፍ ከፀደይ ወር ጋር የደስታ ሥቃይ ያሳልፋል። ክርታታ ኮከቦች ጋር በምሥጢር ይነጋገራል። ዛሬ ግን ለገሞራውም ቢሆን ወሩ ሌላ ወር ነው። ባራት ዓመት አንድ ጊዜ የሚመጣ የፀደይ ወር ብቻ። አዲስ ቀን። አዲስ ሌሊት። አዲስ ዓለም። መግደል የማይቻልበት፣ ሞት የሚሸነፍበት ስዉር ሌሊት ነበር-ሌሊቱ። በመኻል ሀገርም

እሱ እንዳለው ያ ሎሬቱ።

ሞትም ይሙት የታባቱ።"

ሲል ጠቢቡ ያዜመለት ወር ይህ የፀደይ ወር ነው። ጠቢቡ ግን ይህንን ምሥጢር አውቆ የልቡን ይንገረን ወይም በዘፈቀደ ያንጎራጉረው የታወቀ ነገር የለም። ዜማው ለዚህ ወር ታስቦ የተደረሰ ዜማ ከሆነ ገሞራውና የሙዚቃው ሊቅ በአካል ሳይተዋወቁ በምሥጢር ተግባብተዋል ማለት ነው። ያ ካልሆነ ደግሞ ገሞራው ጠልቆ በማወቅ፣ ከያኒው በዘፈቀደ በማዜም ተላልፈዋል። ቀኝም ነፈሰ ግራ የፀደይ ወር እስኳላ

ተማሪዎች ፈተና የሚወስዱበት የፀደይ ወር ሲሆን ገሞራውና ታሪኩ ደግሞ መልእክ-ሞትን የሚገዘቱበት የተለየ ወር ነው። ቀኑም የተለየ ቀን ነው። ዓመቱ ሁለት ሺህ ዐሥራ ሦስት ዓመተ ምሕረት ሲሆን ሐመል የሚባለው የፀደይ ኮከብ ከተወለደ ዐሥራ ሰባተኛ ቀኑን ይዟል። የፀደይ ጨረቃ ከተወለደች ግን የመጀመሪያ ቀን ነበር። በዚች ምሽት ሁለቱ ከርታታዎች ወደሴቶች የስዋሬ ዓለም የሚገቡበት ሰዓት ስለደረሰ ከርታታ ኮከቦች ወደ ሴቶች የስዋሬ ዓለም ማዝገም ጀመሩ። እንደ ልማዳቸው እየተንከራተቱ ወደ ሴቶች የስዋሬ ዓለም ሲያመሩ ቀለሙ ተፈሪ ከፊት ከፊት፣ ደቀኛው ከኋላ ከኋላ ይከተላሉ። ወይራውና ጠቢቡ ሖረ በቀኝ በግራ አጅበዋቸዋል። እያዘገሙ አጭር ማብራሪያ ይቀበሉ ዘንድ ወደ ደቀኛው ዞሩ። ደቀኛው ወደሴቶች የስዋሬ ዓለም ለሚገቡ ሲቆች ማብራሪያ በመስጠት ይታወቃሉ። አሁንም መና መጋገሩን አቋርጠው፣ ከእርምጃቸው ቀንሰው ባጭሩ ስለሴቶች ጠባይ መግለጥ ጀመሩ።

"የስዋሬው ዓለም ሴቶች እንደእኛ ሰዎች ሲሆኑ እንደመኻል ሀገር ከፊል ሴቶች ሴሰኞች አይደሉም። ፍቅር ግን ልበ ቢስ ያደርጋቸዋል። ወንዶች ግን በተፈጥሮ ይሁን በሌላ ነገር ልበ ቢስ ቢጤ ናቸው። ወደ ሴቶች የስዋሬ ዓለም ስትገቡ ለጊዜው ልበ ቢስ ወንዶች "አዳም አዳም





ሸተተን። ሌላ አዳም ወደዚህ ቤታችን ገብቷል" ብለው ባለሁለት ልሳን ጦራቸውን በእሳት አግመው ሊወጓችሁ መንጎራደድ ይጀምራሉ። በዚህ ጊዜ መፍራት የለባችሁም። ሴቶች ውኃ በገበታ አድርገው ትኩሱን ጦር ከውኃው ሲነክሩት ንዴታቸው እንደጦሩ ይበርዳል። ለጥቆ መንጎራደዱን እንዲያቆሙ ገንፎ ያቀርቡላቸዋል። ተመግበው እንዳበቁ ልበ-ቢስ ይሆናሉ። ከዚህ በኋላ ከእናንተ ጋር ያስተዋውቋችኋል። ልበ ቢስ ስለሆኑ ወንዶች በሴቶች መቅናቱን ወዲያኑ ያቆማሉ። ይህ የልበ ቢስ ወንዶች ጠባይ ነው።" አሉ ደቀኛው ትንፋሽ ቆጥበው ጥቂት ራመድ ራመድ እያሉ። አሁን ከሴቶች የስዋሬ ዓለም ሊገቡ የዐሥር ደቂቃ መንገድ ብቻ ቀርቷቸዋል። ጥቂት እንደተራመዱ

"ለጥቆ ሴቶች ከእነሱ የመረጣችኋትን አግብታችሁ እንድትኖሩ ጥያቄ ያቀርባሉ። ከርታታ ኮከቦች ነን በሏቸው። ከርታታ ኮከቦች ነን ስትሏቸው እንደተዋነይ ወደመኻል ሀገር መመለስ እንደምትፈልጉ እየነገራችኋቸው እንደሆነ ያውቃሉ፡ ፡ ፍቅራቸው ከዚህ ላይ ያበቃል። ፍቅር በልመና የማይሆን ነገር እንደሆነ ፈጥኖ በመረዳት ከእነሱ የሚደርስ ፍጡር የለም። ቁርጥ ሲያውቁ ከኅብስተ መናው ሰጥተው ወደ እኛ ይመልሷችኋል። ከመናው ዐፊር ይዛችሁ ወደ እኔ ትመጣላችሁ። እኔ እጋግርላችኋለሁ።

መናውን ትቋደሳላችሁ። ሞት ከዚህ ላይ ይሞታል። ከዐራት ዐይናው አቡሻህር እየተማራችሁ አብረን እንኖራለን። አስፈላጊ ሲሆን ወደመኻል ሀገር ብቅ እያላችሁ ሀገራዊ የጥበብ መጻሕፍትን ወደስዉሩ ዓለም ታመጣላችሁ። ይህ ትውልድ ጥበባችንን በነተበ አቦጀዱ፣ በነቀዘ ስንዴ እንዳይሸጣቸው ማለቴ ነው።" አሉ መና ጋጋሪው።

ታሪኩ ከመናው ዐፈር ይዛችሁ ወደእኔ ትመጣላችሁ። እኔ እጋግርላችኋለሁ ያሉት ንግግር ግራ አጋብቶት

"ኀብስተ መናው ድንጋይ መስሎኝ? የምድር ዐፈር ነው እንዴ? ዐፈር ደግሞ እንዴት ሆኖ መና ይሆናል?" አለ።

"ይሆናል! ይሆናል! ይሆናል ልጄ!" ብለው ድንጋይ መሳይ ድቡልቡል ነገር ከኪሳቸው መዥለጠው

"ይቺ የኑግ ልጥልጥ የመሰለች ድቡልቡል ነገር ድንጋይ አይደለችም። የአፈር ዝርያ ናት። ለምለም ዐፈር ናት። ይች አፈር ባመት አንድ ቀን ከከርሠ ምድር ወደላይ ተነፍታ ወጥታ ትቆለላች። ፍልፈል እንደገፋው ዐፈር ከመሬት ወጥታ ትከመራለች። ስትወጣ መዓዛዋ ስዉሩን ዓለም ያውደዋል። ሴቶች ስፍራዋን ለይተው ያውቁታል። ልበ ቢሶችን ጨምሮ እኛ ወንዶች ግን አናውቃትም። ለሴቶች ብቻ





ፈጣሪ የገለጠው ምሥጢር መሰለኝ። በሴቶች አነጋገር ዐፈሯ ከከርሠ ምድር ወጥታ የምትከመረው በጌታ ቀን ብቻ ነው። የስዉሩ ዓለም ሴቶች ይቺን የጌታ ቀን ሲጠብቁ ከርመው በዚች ቀን ብቻ ትኩሷን ዐፈር ከመሬት ያፍሷታል። ወዲያው ዐፈሯ ኳ ኮርኳ ብላ ትደርቃለች። የሆነ ነገር ይጨምሩባታል። ምን እንደሆነ ከሴቶች በቀር የሚያውቀው ወንድ የለም። በግምት ግን ወንዶችን "ልበ ቢስ" የሚያደርጉበት ምሥጢር ይመስለኛል። ሴቶቹ ግን ቢሞቱ አይናገሩም።" ካሉ በኋላ

"አፈሯ ስትደርቅ በሙቀጫ ወቅጠው እንደኑግ ልጥልጥ ጠፍጥፈው እንደገጠር ወፍጮ መጅ አድቦልቡለው ይይዟታል። ስንትና ስንት ውጣ ውረድ አልፎ ስዉሩን ዓለም ለተቀላቀለ፣ ወንድ ሴቶች መርቀው ይሰጡታል። ከዚያ ዓመት እስከ ዓመት የመና ቁራሽ ሆና በምጣድ ትጋገራለች። ያችን የቀመሰ ሐሽማል ይሆናል። እንደ ተዋነይ መልአክ ሞትን ገዝቶ በሕይወት ይኖራል። ሞት ሲያምረው ከመናው መቅመስ ያቆማል። ከዚህ ስዉር ዓለም ተሰናብቶ ይሄዳል። የሞት ጽዋ ትጠብቀዋለች። "ይች ጽዋ ከእኔ ትለፍ ማለት አይችልም።" ሲሉ ገሞራው ከማድነቅ በቀር ምላሱ በምላጭ እንደተጎመደ ደለደመ። በውስጡ ግን እየተደመመ ነበር። ከዚያም አከሉበት።

“እስከ ዛሬ የደከማችሁትን ድካም ከልፋት አትቁጠሩት፡፡ አሁን አሁን ቀረ እንጂ ድሮ የተዋነይን ጥበብ ፍሰጋ ያልደከመ የቆሎ ተማሪ የለም፡፡ እኔም ወደስዉሩ ዓለም ከመምጣቴ ቀደም ብሎ አንዳንድ ሰዋራ ሰዋራ ስፍራዎችን ዘወር ዘወር ብዬ ለማየት በቅቻለሁ፡፡ በእርግጥ ያን ጊዜ የለፋሁት ልፋት መልካም ፍሬ አፍርቷል ማለት ይቻላል፡፡ ወደዚህ ዓለም ከመምጣቴ በፊት ሆድ ቁርጠት ነበረብኝ፡፡ እርም አድርጎ ተወኝ፡፡ በተለይ ጭንቀት እንደቆላ ጠላ ከናላዬ ወጥቶ ነበር፡፡ ቀስ በቀስ ረገበ፡፡” አሉ ደቀኛው፡፡

“እረ ሁላችንም የነዘር እባብ ሲሳይ ሆነን ነው መናውን ያገኘነው! ከጠቢቡ ሖረ በቀር ወደስዉሩ ዓለም በደመና ተጭኖ የገባ የለም፡፡ ወይራውም የማኅበረ ሥላሴ ገዳም አኸያ ጫኝ ነበሩ፡፡ ከማኅበረ ሥላሴ እስከ ጎንደር አኸያ እየጫኑ በልፋት ኑረው ነው ወደዚህ የመጡት፡፡ እኔም እንጂ እንደአቅሜ ከፊል ኢትዮጵያን አዳርሻለሁ፡፡ ከቦሩ ሥላሴ ከወጣሁ በኋላ ለቅኔ ትምህርት ከትግራይ እስከ ጎንደር፣ ከሸዋ እስከ ጎጃም ዳክሬአለሁ፡፡ ለአቡሻህር ቀመር ደብረ ቢዘን ለብሉይ አክሱም ጽዮንን ተሳልሜአለሁ፡፡ ያን ሁሉ ውጣ ውረድ ጨርሼ ወደቦሩ ሥላሴ እመለሳለሁ በዚያም አካለወልድን ተክቼ የቀለም ቀንድ እሆናለሁ የሚል ተስፋ ነበረኝ፡፡ ኪነ ጥበብና ሊቁ ፋሬስ ዘጎንጅ አምጥተው ጥለውኝ ሄዱ፡፡ ከዚሁ ቀረሁ፡፡ አሁን ኪነ ጥበብ በሕይወት የለም፡፡ ፋሬስ ግን ሐሽማል ሲሆኑ የሚፈልጋቸውን ፍሬ ፍሬ የአብነት ተማሪዎች እየሳከ ነው፡፡” አለ ቀለሙ ተፈሪ፡፡





ከዚያ ደቀኛው ተቀብለው ቀጠሉ፡፡

“አዎን! እኔም በመጀመሪያ የዞርሁት ድፍን ጎንደርን ነበር፡፡ የተዋነይ ልብስ ከጎንደር ይኖራል ብለውኝ ለስድስት ዓመት ድፍን ጎንደርን እንቧለሌ ዞርኋት፡፡ በሰባተኛው ዓመት ስፍራውን ደረስሁበት፡፡ ሀገረ ሰላም ውዶ ማርያም ይባላል፡፡ ካህናቱ አንድ ቁራጭ ወንጨሬ ሉሪ አውጥተው የተዋነይ ልብስ ማለት ይኸው ነው ብለው በምሥጢር አሳዩኝ፡፡ ስእል ነበር፡፡ ከልብሱ ላይ “ኅብስተ መና” የሚል ጽሐፍ በረቂቅ ተጽፎበታል፡፡ በውስጤ ቋጥሬ ፍችውን ሳፈላልግ ኅብስተ መና የሚል ጽሑፍ የመናው ቁራሽ መሆኑን አንድ ሊቅ ተረጎሙልኝ፡፡ ይህን ስፍራም እንደዋዛ አመለከቱኝ፡፡ ሰተት ብዬ መጣሁ፡፡ ከእኔ በፊት ባራቱ የሀገራችን ክፍል የመጡ ሊቆች እኔ እንዳልገባ ተከላከሉ፡፡ እንደምንም ታግዬ በጭንቅ ገባሁ፡፡ እኔ ከገባሁ በኋላ አዲስ ሕግ ወጣ፡፡” አሉ ደቀኛው በኋላ በኋላ እየተከተሉ፡፡

“ምን የሚል ሕግ?” አለ ታሪኩ፡፡

“በፊት ኀብስተ መናውን የሚጋግሩ እንደ ባህሉ ሴቶች ነበሩ። እኔ የገባሁ ሰሞን ሴቶች መና ከመጋገር ወጥተው እንደፈለጉት ይኑሩ። መና ጋጋሪዎች ወንዶች ይሁኑ የሚል አዲስ ሕግ ወጣ። እንደሚታወቀው ደቅ የሴቶች ርስት ነው። ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ይበዛሉ። ከሴቶች አንጻር እኛ ወንዶች ተቀጽላዎች ነን። ሴት ከወንድ ጎን እንደፈለቀች ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል። በዚህ ስዉር ዓለም ግን ወንዶች ከሴቶች እግር ሥር ይፈልቁ ይመስል ሴቶች ብዙ፣ ወንዶች ጥቂቶች ናቸው።” አሉ ደቀኛው ከሴቶች የስዋሬ ዓለም ሊገቡ የመጨረሻው በር ሲደርሱ።

“አልገባኝም?” አለ ታሪኩ።

“ተው እንጂ እያደረ ጥሬ አትሁን። ዐራት ዐይናው ስንትና ስንት ደክመው አስተምረው ወደኋላ ትመለሳለህ እንዴ? አታጋልጠኝ ነው ማለት እናንተዩ! ታሪክ እንደሚጠቁመው ደቅ የኩሻውያን ቦታ ነው። ኩሻውያን ሴቶችና ወንዶች መጥተው በዚህ ስፍራ ሠፈሩ። ወንዶችም ሴቶችም ጠቢባን ነበሩ። በቁጥር ከወንዶች ሴቶች ይልቃሉ ይባላል። ቀስ በቀስ ሐበሾች ተቀላቀሉ። ተዋለዱ። ተዛመዱ። በሥጋ ተጋመዱ። በፊት ግን በዚህ ውስጥ ከነበሩ ሰዎች አብዛኞቹ ኩሻውያን ጠቢባን ነበሩ። ከመሰውር ጀምሮ ሌላው ቅራቅንቦው ጥበብ





ጭምር ነበራቸው። ነገር ግን መናው ቀርቶ የሐበሻ እንጀራ ጋግረው መብላት አያውቁም ነበር። በዚህ ሕላዌ እያሉ ተራቡ። ሴቶች የምድሩን ትተው በሥነ ፈለክ ጥበብ ላይ ተፈላሰፉ። ከፍልስፍናቸው ቀዳሚ የሚበሉና የማይበሉ ዐፈሮችን መመርመር ነበር። በዚሁ ጫካ ውስጥ ካለው ፍራፍሬ እየተመገቡ በዐፈሩ ላይ ሲመራመሩ የኀብስተ መናን ምሥጢር ደረሱበት።” አሉ ደቀኛውም አሁንም በሩ ላይ እንደቆሙ።

“እንዴት አድርገው?” አለ ገሞራው።

“ይች ዐፈር መቼ ወር እንደምትወጣ ለማወቅ ሴቶች የሚያውቋት እኛ ወንዶች የማናውቃት የዕፅ ፍሬ አለች። በመጀመሪያ በስዉሩ ዓለም የነበሩ ሰዎች ፍሬዋን በአፈር ውስጥ ቀብረው ውኃ ያጠጧት ጀመር። በዐሥራ ሁለቱ ወራት፣ በሦስት መቶ ሥልሳ አምስት ዕለታት ልክ ሦስት መቶ ሥልሳ ፍሬዎች መርጠው በየቀኑ አንዳንድ ፍሬ ተከሉ። ከመስከረም እስከ መጋቢት ድረስ የተከሏቸው ፍሬዎች ዐመድ ሆነው ቀሩ። መጋቢት ዐሥራ ስድስት ቀን ሐመል የሚባለው ኮከብ ሲወለድ ድጋሜ መትከል ጀመሩ። ከመጋቢት ዐሥራ ስድስት ቀን ጀምሮ ያችን የጌታን ቀን እስኪያገኙ ድረስ እየተከሉ ቀጠሉ። በጌታ ቀን ግን ፍሬዋ

ከስም ዐፈሯ ከመሬት ወጥቶ ወጥቶ እንደ መደብ ተቆለለ፡፡ ወደማታ ዐፈሩ መድረቅ ሲጀምር አፍሰው አስቀመጡት፡፡ እንጀራ ይሆናል የሚል ግምት ግን አልነበራቸውም፡፡ ሐሳባቸው እንደማኛውም ለምለም ዐፈር ለምርምር ይውላል ነበር፡፡" ካሉ በኋላ ቀጠሉ፡፡

"ዐፈሩ በደንብ ሲደርቅ እሳት ላይ ጣል ቢያደርጉት ትኩስ መና ሆኖ መዓዛው ያውዳቸው ጀመር፡፡ መዓዛው ሲጣፍጣቸው ሴቶችና ቀደምት ጠቢባን መናውን በመቅመስ ለማረጋገጥ ፈለጉ፡፡ ነገር ግን መጀመሪያ ማን ደፍሮ ይቅመሰው? ጠቢባኑ አንተ ቅመስ አንተ ቅመስ እየተባባሉ ተገዳገዱ፡፡ በኋላ በአራዊት ለመፈተን ለአንድ ዥንጀሮ ወረወሩለት፡፡ ከሰማይ ቀልቦ ሲጎርሰው ከቋንቋ በቀር ሰውኛ ጠባይ አመጣ፡፡ ጠባዩ እንጂ አውሬነቱ ግን አልተለወጠም፡፡ በጠባዩ ለውጥ አምጥቶ ከሰው ጋር መዋል ማደር ሲጀምር ግራ ተጋቡ፡፡ በኋላ አንዲት ሴት አፈቀረ፡፡ ሊገድሉት ቢቀጠቅጡት ቢቀጠቅጡት የማይሞት ሆነ፡፡ ጠቢባኑ በዚህ ግራ ገባቸው፡፡ ቀስ በቀስ ይህ ዐፈር የመልአከ ሞት መድኃኒት ሊሆን ይችላል ወደሚል ሐሳብ መጡ፡፡ ከመካከላቸው በእድሜ ገፋ ያለች አሮጊት ነበረች፡፡ ብሞትም እድሜዬ ገፍቷል፡፡ ብታመም ታስታምሙኛላችሁ ብላ ከዐፈሩ ልጥልጥ ጋግራ ቆርሳ ቀመሰች፡፡" ብለው ዝም ሲሉ





"ከዚያስ?" አለ ታሪኩ

"ምን ልበልህ? መናው ተስማማት፡፡ መልኳ በራ፡፡ የተጨማደደ ፊቷ ተፍታታ፡፡ ውበቷ ከወጣት ሴቶች በላይ ፈካ፡፡ ከፀደይ ጨረቃ ውበት ተካከለ፡፡ ሌሎች ሴቶች ዐፈሩን ጋግረው መናውን ተካፍለው መመገብ ቀጠሉ፡፡ የዕለት ራታቸው መናው ሆነ፡፡ ሴቶች በተራ በተራ ቀን ተካፍለው ልጥልጡን ዐፈር ከምጣዱ ላይ ጣል እያደረጉ መጋገሩን ቀጠሉ፡፡ እንደምታውቁት ባረጀው ባሕል መሠራት እንጀራ መጋገር የሴቶች ሥራ ነበር፡፡ እኒህ ሴቶች በደቅ ውስጥ ሆነው እንጀራ በመጋገር ተጠመዱ፡፡ መናው ከመናነቱ ጎን ለጎን የሞት መግቻ መሆኑ ተረጋገጠ፡፡ ይህ ዓለም የጠቢባን ዓለም ሆኖ ቀጠለ፡፡ ከጊዜያት በኋላ ግን በወንዶችና በሴቶች መካከል ግብግብ ተፈጠረ፡፡" አሉ ደቀኛው፡፡

"በምን ምክንያት?" አለ ታሪኩ፡፡

"ኩሻውያን ወንዶች ልበ ቢስ ሆነው ቀጠሉ፡፡ ከሴቶች ጋር ለመኖር የሌሊቱን ምሥጢር በሴቶች ፍላጎት ልክ መፈጸም የማይቻላቸው ሆኑ ልበ-ቢስ ወንዶች፡፡ ሴቶች ከደቅ ተነሥተው ወደ መኻል ሀገር እየሄዱ መቅረት ጀመሩ፡፡ ከደቅ ሲወጡ ይህንን ምሥጢር ጭምር ይዘው ወጥተው በመኻል ሀገር እንደ ጨው ነሰነሱት፡፡ ከጊዜያት በኋላ ቀደምት ጠቢባን

ጉባኤ ሠሩ። በመፍትሔው ዙሪያ መከሩ። ከብዙ ክርክር በኋላ ሴቶች ከዚያ ማዶ አግብተው ተጋብተው እንዲኖሩ ተወሰነ። ጋብቻው ቢፈቅድም ወንድ ግን ሲያገኙ አልቻሉም። ይህ ነገር ድጋሜ ጭቅጭቅ ፈጠረ። በዚህ ያሉ ጠቢባን ከሴት ጋር ለመኖር ፈቃደኛ ባለ መሆናቸው ሴቶች ወደ መኻል ሀገር ሂደው የወደዱትን ወንድ ወደዚህ ዓለም አምጥተው በትዳር እንዲኖሩ ተወሰነ። ሴቶች ወደ መኻል ሀገር ብቅ እያሉ በድንግልና የሚኖር ወጣት መምረጥ ጀመሩ። በወቅቱ በድንግልና ጸንተው የሚኖሩ የቆሎ ተማሪዎች ተገኙ። ሸበላ ሸበላውን የቅኔ ተማሪ እየመረጡ ወደ ደቅ ማምጣት ጀመሩ። በዚህ መና ድግስ ደግሰው ጋብቻ ፈጸሙ። ይህን አድርገው ልጅ እየወለዱ በዚህ ውስጥ መና እየጋገሩ ይኖሩ ነበር። እየቆዩ ልጆቻቸው ይህን ምሥጢር ይዘው ወደ ከተማ እየሄዱ መቅረት አመጡ። ከሴቶች በኩል መና መጋገር ተከለከለ። ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ ውሳኔው ጸደቀ። ሴቶች ቀርተው እኛ ወንዶች መና ጋጋሪ እንድንሆን ተወሰነ። እኔ ተመረጥሁ። ከሴቶች መና መጋገር ተምሬ ይኸው ዛሬ ድረስ መና ጋጋሪ ነኝ።" ብለው ፈገግ አሉ።

"ጥሩ ነው። ባይሆን እርስዎ መጋገር ብቻ ነው። አባ ኮስትር በላይ ዘለቀ ግን ጤፍ ሳይቀር እየፈጨ እንጀራ እየጋገሬ





አርበኞችን መግቧል። ስለዚህ ከአባ ኮስትር ከፊሉን ሥራ ተወጥተዋል።" አለ ገሞራው እየሳቀ።

"ለምን ነበር ልጁ በላይ ዘለቀ ጤፍ የፈጨበት ምክንያት?" አሉ የተለመደው የአባ ኮስትር ታሪክ ግር ብሏቸው። ከሴቶች የስዋሬ ዓለም በር ላይ እንደቆሙ።

"አባ ኮስትር ለምጩን ሳይ ሳለ የሠራዊቱ ቀለብ አለቀበት። ወደ ቢቸና ዘልቆ ቀለብ እንዳያመጣ ጣሊያን ባንዳዎችን ጨምሮ እንደሾኽ ተከስክሶ የማያላውሰው ሆነ። አንድ ክምር ጤፍ ወቅቶ በልሙጥ ድንጋይ እንዲፈጩ ለተከታዮቹ ትእዛዝ ሰጠ። በወቅቱ እሳቤ ሴት ደካማ ፍጡር ሆና ትሳል ስለነበር በረሐብ እናልቃለን እንጅ እንደሴት ጤፍ አንፈጭም ሲሉ ተከታዮቹ ለገሙበት። አባ ኮስትር ኮስተር ብሎ የጎጃምን ነጭ ጤፍ ሲፈጭ ሽብረክ አለ። ጣሊያንን እያንበረከከ አባ ኮስተር ጤፍ ለመሰለቅ ሲንበረከክ ያየ ባለቅኔ

"ያባቱን ጩርሼ የእናቱን ይጃለሁ።

ለምጩን ከበሩ ላይ ጤፌን እፈጫለሁ።"

ሲል አዘመረለት። የአባ ኮስትር ሥራ ይቺው ናት።" ገሞራው በአእምሮው የመጣለትን የአባ ኮስትርን ታሪክ ቆንጽሎ ተናግሮ ዝም ሲል



Scanned with CamScanner

“ሊቅ! ሊቅ! ሀገራዊ ታሪክም በጆሮህ ነፍሶብኻል። ብዙ ቁሶች ለመንፈሳዊው ታሪክ እንጂ ለሀገራዊ ታሪክ እምብዛም ናቸው። ከኢትዮጵያ ታሪክ ይልቅ ለግብፅ ታሪክ ያደላሉ። ከቅዱስ መጽሐፍ ለጥቆ ከብሉይና ከሐዲስ የተቀዳ የይሁዲ ወግና ባሕል ያውቃሉ። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ግብፅ መሠረታዊ ጠላታችን እንደ ሆነች ግን ልብ ብለው አያውቁም። በመንፈሳዊ በኩል “ማርቆስ አባታችን እስክንድርያ እናታችን” ብትሆንም የዓባይ ልጆች እንደ መሆናችን ግን ግብፅ ጠላታችን ናት። ሱዳን ደግሞ የጠላታችን ወዳጅ ናት። ሁለቱም የኢትዮጵያን ሥልጣኔ አጥብቀው ይጠላሉ። ጥላቻቸው አሁን ዓለም በሰለጠነበት ዘመን ጭምር ጎልቶ ይታያል። በተለይ ከፊል ግብጻውያን ከፈርዖናውያን እስከአሁኑ መሪ ድረስ ሕልማቸው የኢትዮጵያን ሥልጣኔ መቅበር ይመስላል። በጥበብ እንደ ምንበልጣቸው ግን ልብ ያሉ አይመስሉም። ከፊል የሀገሬ ሰነፍ ቀሳውስት ልብ ብለውት አያውቁም። እኔ ግን እንደጥንቱ “ማርቆስ አባታችን እስክንድርያ እናታችን”ን በሚለው ሃይማኖታዊ ሐሳብ ባምንም አሁን ግን “ግብፅ ጠላቴ፣ ወንጌላዊ ማርቆስ አባቴ” እያልሁ መዘመር ጀምሬአለሁ። እስክንድርያ እናታችን የሚለውን ቃል “ኢትዮጵያ እናታችን” በሚል ብርቅዬ ቃል ተክቸዋለሁ።





በእምነትም ሆነ በተፈጥሮ ከእስክንድርያ ይልቅ ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር የእግሩ መረጋጫ እንደሆነች አጥብቄ አምናለሁ። “እስክንድርያ እናታችን እያሉ ኢትዮጵያ በሚኖሩ ግብዞች መናደድ ጀምሬአለሁ።” ካሉ በኋላ

ደቀኛው ይህን እየነገሯቸው ታሪኩና ገሞራው ግን ከገነት በር ላይ ቆማ አስገቡኝ እያለች የገነትን ጠባቂ መልአክ እንደምትማጸን ነፍስ ሞትን መግዘት ከሚቻልበት በር ላይ ቆመው መግባት አምሯቸው ይቁለጨለጫሉ። ንግግሩን አሳጥረው ፈጥነው እንዲያስገቧቸው ሁለቱም እኩል ማሰባቸውን ዐይናቸው ይመሰክራል። ዐይናቸው ቅምጭው፣ ቅምጭው፤ ቁልጭ፣ ቁልጭ ይላል። “እስከ ዛሬ ከተንጓለልነው ይልቅ የዛሬው ያስጎመጃል። በሩ ላይ ቆሞ መቆየት እጅግ ያንጓል” እያለ ገሞራው በልቡ ሲያወጣ ሲያወርድ ሳለ ደቀኛው ተናገሩ።

“አፈር ናችሁና ወደ አፈር ትመለሳላችሁ።” ሲሉ።

“አሜን! አሜን!” አሉ ጠቢባኑ ባንድ ድምፅ።

“ደግሞ አፈር ናችሁና አፈር በትታችሁ በሕይወት ትኖራላችሁ።” አሉ ድጋሜ።

በዚህ ጊዜ ገሞራውና ታሪኩ ብቻ አሜን እንዲሉ ታዘዙ።



Scanned with CamScanner

ሽብረክ ብለው "አሜን አሜን" አፈር በልተን እንደ ጠቢባኑ በሕይወት እኖራለን።" ሲሉ ደቀኛው ተናገሩ፡፡

"ይበሉ ዐራት ዐይናው ወደ ሴቶች የስዋሬ ዓለም ተቀላቅለው ከመናው ተቋድሰው ሞትን ገዝተው ሐሽግል ሆነው ከእኛ ጋር በሕይወት ይኖሩ ዘንድ በሩን ይከፈቱላቸው፡፡ ወደፊት ኢትዮጵያ ትፈልጋቸዋለች፡፡" ደቀኛው የመጨረሻውን ንግግር ተናግረው ወደመጡበት ዘወር አሉ፡፡ ዐራት ዐይናው ከሴቶች የስዋሬ ዓለም ከደረሱ በኋላ ወደጎን ቆመው ከርታታ ኮከቦችን ወደውስጥ ላኳቸው፡፡ ገሞራውና ታሪኩ የሴቶችን ድምፅ እየሰሙ ወደፊት ገሰገሱ፡፡ የፀደይ ጨረቃ ሌሊቱን ሞሽራዋለች፡፡ ድቅድቁን የደቅ ጫካ የጨረቃ ውበት ፈሶበታል፡፡ ገሞራውና ታሪኩ ከመናው ተቋድሰው ሐሽግል ሊሆኑ ወደ ሴቶች የስዋሬ ዓለም ሲዘልቁ ደቀኛው፣ ዐራት ዐይናው፣ ወይራው ጠቢቡ ሖረ በፍሥሓ ሰከሩ...፡፡





ኪነት በዮዲ(@gbw_dan)
የቴሌግራም ቻናል



Scanned with CamScanner

ኪነት በዮዲ(@gbw_dan)
Telegran Chanel
ኪነት በዮዲ(@gbw_dan)